Newsletter
V.1 No. 1

# Ethiopian Federal Charities and Societies Forum

© Copy right 2014

Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF)
Phone: 0118675939 / 251-920-863714
Fax: 0116638127
E-mail: fcsf2005@gmail.com
info@fcsf.net
www.fcsf.net
Djibouti Street, behind St. Gabriel Hospital
P.o.Box: 4408 Addis Ababa, Ethiopia.

Edited by

Negash Teklu
Wubeshet T/mariam
Tigabu Haile

Prepared by

Yetneberish Nigussie
Eshetu Bekele (Dr.)
Wubeshet T/mariam

Produced by Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF) with the support of Civil Society Support Program (CSSP).

# Table of contents


1. Chairperson's Notes ........................................................... 5
2. Progress Report Digest .......................................................6
3. የአንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት .................................10
   3.1. የመድረኩ የእስካሁኑ የስራ ክንውን ሪፖርትና በስራ ክንውኑ ላይ የተደረገ ውይይት......................................12
   3.2. በተሻሻለው የመድረኩ ዝክረ-ነገር (ToR) ላይ የቀረበ ማብራሪያና በዝክረ-ነገሩ ላይ የተደረገ ውይይት.........16
   3.3. በመድረኩ የ2014 ድርጊት መርሀግብር ላይ የቀረበ ማብራሪያና በድርጊት መርሀግብሩ ላይ የተደረገ ውይይት.....20
   3.4. የመድረኩን አርማ ለጉባኤው ማቅረብና ውይይት በማድረግ የማጽደቅ ሂደት.................................................22
   3.5. በጎደሉ የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የንኡሳን ኮሚቴ አባላት ምርጫ.........................................................23
   3.6. በኢፌዲሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተዘጋጁ ወጪ መጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ.............24
4. Statute of the Forum .........................................................26
5. Annual action plan of the Forum .......................................34
6. List of participants ...........................................................40
7. Forum Recognition Letter from CSA...................................41

# Chairperson's Note

Dear EFCSF members and partners,

Greetings and welcome to the first edition of the Ethiopian Federal Charities and Societies Forum Newsletter! This News Letter is in Amharic and English, covering how and why we were established, our activities, achievements and the process we came since our establishment in May 2013, and also addresses, where we are at this stage and our counting activities and engagemantes.

In Ethiopia, within the CSO sector there are above 3000 local, resident and international charities and societies organizations registered at federal level, where around 54 are consortiums or networks, and above 2000 registered at regional level. But, despite their number, these three types of charities and societies have not had a forum similar to the business community which the Chamber of Commerce is mandated, in raising common concerns and values, formal representation and coordination of the sector. Therefore, looking to the contribution of the charities and societies sector in development of the country and the strong partnership and harmonization needed among its social base, members and government, establishing the forum formally was highly important and timely. In general, the Forum shall mainly be responsible for facilitating the collaborative and complementary engagements of Charities and Societies Organisations (ChSOs) towards the creation of the necessary systems and infrastructures conducive for the affairs of as well as meaningful participation of ChSOs in the development of the nation.

In the last one year it was possible to establish the Forum by having its stablishment and First Members General Assembly represented from the local, resident and international organisations where majority are consortium or network representatives and participants from those not incorporated within the networks/consortiums being delegated by grouped associations mainly from regions. Through those assemblies it was possible to reach agreement on the statute, name of the Forum, its logo, activity plan, and have elected the seven Executive Committee and subcommittee members. The Forum now is with its office being hosted at VSO, its bank account and website http://www.fcsf.net. Throughout the process the support from the Federal Charities and Societies Agency and donors like the Irish Aid led donor group (like DFID, Netherlands, Sweden, Norway, and Canada) through CSSP and EU's support was very helpful and highly appreciated.

In the coming follow up engagement and activities as indicated in the activity plan the main focus of the Forum will be in reaching to more member networks/consortiums and the charities and societies in general at federal and regional level in a way they have clarity on the process, and complement each other, own the values of the Forum, so that the charities and societies voice is well organized and heard, partnership with government at all levels is well harmonized accountable, and trust is created and contribution of the charities and societies in development is scaled up and recognised.

Wishing you nice reading.

Negash Teklu
Executive Director of PHEEC,
Chairperson of EFCSF

# Progress Report Digest

Whilst charity work has long been recognised as part of the traditional social fabric and economic mainstay of the Ethiopian society, until the early 1990s the Charities and Societies sector, in its modern form, consisted of a small number of organisations and they have operated under difficult and sometimes trying circumstances. Both the imperial and the Derg regimes were unwilling to allow independent Non-Governmental Civil Society Organisations (CSOs) but they were forced by pressing environmental disasters and human crisis, such as droughts and famines, to allow Non-Governmental Organizations (NGOs), of which most were foreign organisations and faith based local groups, to engage in relief operations.

However, it is following the fall of the Derg regime in 1991, which brought a change of government and the new constitution, which clearly provided the freedom of association, that the Charities and Societies sector has seen significant growth both in terms of numbers and diversity, and has become formalized. Thus new Charities and Societies Organisations (ChSOs) with diverse development agendas; associations with the constituency of women, youth, disability and other groups; professional associations; as well as Consortiums and Networks of ChSOs started to flourish and expanded their presence and scope of operational engagement in the country, from Federal to Regional, Zonal and Woreda levels. The total number of ChSOs registered by the Charities and Societies Agency (ChSA) at Federal level is estimated at 3067 with an additional estimated 2000 registered at regional levels bringing the total number of ChSOs operating in Ethiopia to an estimated over 5000.

As the ChSOs sector has grown in numbers, diversified and expanded its operational and areas of public engagement, it has gained increasing recognition and support from many quarters, including government, donors, and the public at large. The Charities and Societies Proclamation, Number 621/2009, has furthermore provided the legal, operational and institutional frameworks in order "to ensure citizens right to association enshrined in the country's constitution and to facilitate the role of Charities and Societies in the overall development of Ethiopian peoples" (Charities and Societies Proclamation, Number 621/2009). It is also acknowledged that many of the progresses made and achievements gained in poverty reduction and other development successes in Ethiopia over the past decade were due, in part, to the contributions of ChSOs.

The five-year Growth and Transformation Plan (GTP 2011 – 2015) and the attainment of poverty reduction and sustainable development in general call for partnerships and harnessing the combined efforts of all development partners and stakeholders, including ChSOs. In order to maximise the effectiveness and efficiency of their roles in and contributions towards poverty reduction and sustainable development, and recognising the need to reinvigorate their collaborative engagements, partnerships, coordination and networking, the Consortiums and Networks of ChSOs operating in Ethiopia have together and established the **Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF) in May 2013 with the following purposes.**

➤ To establish a formal non-statutory institutional arrangement whereby Charities and Societies Organisations (ChSOs) actively participate in coordinating, collaborating, networking, facilitating and supervising a range of initiatives aimed at strengthening and maintaining conducive enabling environment for their effective engagement in and contribution towards the national development endeavours.

➤ To establish an institutional arrangement and platform which ensures the effective administration, management and representation of Charities and Societies Organisations (ChSOs) registered and operating in Ethiopia.

➤ To put in place the foundation for the establishment of necessary arrangements guiding the interactions between Charities and Societies Organisations (ChSOs), government bodies and other relevant stakeholders.

The Forum's operational scope is with a focus on institutional and operational issues and processes that commonly concern the Charities and Societies sector in Ethiopia. In general, the Forum shall mainly be responsible for facilitating the collaborative engagements of Charities and Societies Organisations (ChSOs) towards the creation of the necessary systems and infrastructures conducive for the affairs of as well as meaningful participation of ChSOs in the development of the nation. More specifically, the main roles and responsibilities of the Forum are;

➤Facilitate the establishment of an enabling environment regarding the affairs of Charities and Societies at all levels of engagement.

➤Promote the value of vibrant and effective Charities and Societies for bringing about sustainable development of the country.

➤Create information and knowledge base on all pertinent issues of Charities and Societies at comparative and national levels.

➤Facilitate experience and information sharing forums among different stakeholders from the public, donors' community and representatives of Charities and Societies aimed at effective dialogue and coordination regarding the enjoyment of an enabling environment for the sector.

➤Facilitate effective partnership between Charities and Societies and different sector offices of the government.

➤Design and facilitate realization of efforts aimed at putting in place an effective system for following up, monitoring and evaluation of the activities of the forum regarding creation of an enabling environment for Charities and Societies sector.

➤Design and adopt a code of conduct at which Charities and Societies can operate in an ethical and accountable manner.

Deriving its recognition from a special letter of recognition provided by the Federal Charities and Societies Agency (ChSA), EFCSF is a non-partisan, independent, inclusive and voluntary Forum with its constituency (through membership of their Consortiums, Networks and representative ChSOs) being the Charities and Societies Organisations (ChSOs) registered by the ChSA and operating in Ethiopia, in their diversity and configuration. The Forum also recognises the independent existence of various national and regional level ChSO Consortiums and Networks as the bases of its foundation and as an important ChSO coordinating mechanisms with complementary comparative advantages.

**Structure of EFCSF:**

➤General Assembly (GA): A convention comprising of all members of the Forum.

➤Executive Committee: An Executive Committee comprising of the following seven elected members and accountable to the General Assembly (GA) is responsible for leadership and management of the implementation of the strategic and operational plans of the Forum, three of them are members of the Civil Society Support Working Group (CSSWG).

1. **Ato Negash Teklu,** from PHE Ethiopia Consortium, Chairperson.

2. **W/ro Yetnebersh Nigussie** from ECDD, Vice Chairperson

3.**Ato Wubeshet Woldemariam**, from VSO Ethiopia, Secretary.

4. **Ato Alemayehu Bekele** from PANE, Member.

5. **W/ro Azeb Kelemework** from UEWCA, Member.

6. **Ato Holie Fole** from CORHA, Member.

7. **Ato Tigabu Haile** from AMPI, Member.

➤Sub-Committees:

1) Promotion and Accountability,
2) Partnership and Collaborative Engagement, and
3) Research and Dialogue.

➤Secretariat Office:

The Secretariat Office is responsible to effectively execute, coordinate and deliver on the day-to-day activities and tasks of the Forum and provide necessary management and technical expertise and support to the Executive Committee and Sub-Committees.

## Activities Undertaken and Progresses Made:

In order to strengthen the Forum, the Executive Committee has developed and been implementing various important initiatives over the past twelve months. As its first phase initiative, and with financial support from CSSP, the Executive Committee has developed the necessary administrative, operational and institutional frameworks, including Statute, Annual Plan of Action (APA), Logo, official seal, and opening Bank Account of the Forum which have been presented, discussed and endorsed at the second General Assembly (GA) meeting held on 25th February 2014 in Addis Ababa. The Executive Committee is also currently in the process of developing the Forum's website (www.fcsf.net); promotional materials including newsletter, brochures, and articles; as well as facilitating a visit to the Renaissance Dam by representative Consortiums and Networks of ChSOs, chaired by CCRDA. In all those engagments the contribution of the Excutive Committee members was so remarkabley as the Forum was without any secretariat office .

## Next Steps:

Following the development, and endorsement by the first General Assembly (GA), of the Annual Plan of Action (APA 2014/15) and in order to further strengthen the relevance, capacity and effectiveness of the Forum, the Executive Committee is planning to implement a range of initiatives, described below, over the next one – two years for which it is seeking financial resource support, from CSSP, EU and otheres.

**1) Strengthen the promotion, accountability, partnership and collaborative engagement of the Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF) and the Charities and Societies sector in Ethiopia.**

➤Preparing and disseminating promotional materials, such as brochures, newspapers, updates and articles, about the Charities and Societies sector, including successful and best practice projects.

➤Facilitating workshops for consensus on agenda building in all regions and city administrations.

➤Media work – Use of ETV and Radio programmes, Newspapers, and Social Media – to promote and raise the profile of the Charities and Societies sector.

➤Organising conferences/workshops between charities and societies members, high level government officials, partners and relevant stakeholders to facilitate feedback, discussions and sharing of learning based on ChSOs best practice activities.

➤Develop and roll-out a national level Joint Code of Ethics and Conduct (JCEC) of Charities and Societies Organisations (ChSOs) operating in Ethiopia, by complimenting the existing initiatives.

➤To organise and hold a national level Annual Charities and Societies Day/Fair, by complimenting the existing initiatives.

**2) Undertake research, facilitate constructive dialogue, and strengthen the Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF) representation of the Charities and Societies sector in Ethiopia.**

➤Conduct and use existing research outputs on topics relevant to and identified in consultation with members of the Federal Forum and relevant stakeholders.

➤Preparing and disseminating research study reports through publications, conferences/workshops and the Forum website.

➤Organising and facilitating dialogue platforms/conferences for constructive dialogue and discussion between ChSOs and various high level government officials.

➤Representing the ChSOs sector with relevant government bodies, forums and platforms in Ethiopia and abroad with major common issues for representation identified in consultation with members of the Forum

**3) Developing and implementing institutional and operational systems, procedures and frameworks of the Forum.**

➤To develop and implement systems, procedures and policies necessary for the smooth and effective functioning of the Secretariat Office of the Forum .

➤To develop and maintain up to date Website of the Forum and database of members and all ChSOs profiles by category, and thematic and geographical areas of engagement.

➤Developing, finalising and disseminating five-year Strategic Plan of the Forum for the sector.

➤Organising and holding the second and third Annual General Assembly (GA) meeting in Addis Ababa.

➤Mobilise resources and raise funds to enable the sector fully and effectively implement its strategic objectives.

# የአንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ በግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የመድረኩ የመጀመርያው መመስረቻ አጠቃላይ ስብሰባ ማካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡ ይህ መድረክ በኢፌዲሪ በጎ አድራጎትና ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ አስተዳደራዊ እውቅና በማግኘት የቀድሞው ግብረ ኃይል (Task force) ያከናወናቸው የነበሩትን ተግባራት በመተካት በሶስቱም ዘርፎች የሚገኙ ህብረቶች፣ ጥምረቶች፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አማካኝነት የተቋቋመ የጋራ መድረክ ነው፡፡ ይህ መድረክ ሶስቱንም ዘርፎች ማለትም የውጭ፣ የኢትዮጵያ ነዋሪና ኢትዮጵያዊ የሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የሚወክልና በአንድ ላይ የሚያገናኝ እንደመሆኑ መጠን መድረኩ እነዚህ አካላት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች የሚቀርፉበትና መልካም ተሞክሮዎቻቸውን የሚያጎለብቱበት የትብብር መድረክ ነው፡፡

የጠቅላላ ጉባኤው አላማ፡- ጉባኤው አንደኛው የመደረኩ መደበኛ ጉባኤ ሲሆን ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመዳሰስ ቀጣይ አቅጣጫዎችን የሚተልምበት ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ ጉባኤ የተለያዩ አንኳር የመድረኩ ውሳኔዎች የተላለፉበትና በጎደሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምትክ እና የንኡስ ኮሚቴ አባላት ምርጫ የተካሄደበት ነው፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው የተካሄደበት ቀንና ቦታ፡- የካቲት 8 ቀን 2006 ዓ.ም በደሳለኝ ሆቴል አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡

የጠቅላላ ጉባኤው ጠሪ፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ

በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተገኙ ተሳታፊዎች ፡- በአጠቃላይ 43 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል፤ ከዚህም ውስጥ 7ቱ ሴቶች ሲሆኑ 36ቱ ወንድ ተሳታፊዎች ናቸው ፡፡

በጠቅላላ ጉባኤው የተገኙ አካላት፡- በጉባኤው ላይ የመድረኩ አባል የሆኑ ህብረቶች፣ ጥምረቶች፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት፣ አለማቀፍ ለጋሾችና የልማት አጋሮች ተገኝተዋል፡፡

የተወከሉ የመንግስት ኤጀንሲዎችና ሚኒስቴር መስሪያቤቶች፡-
›› የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
›› በኢፌዲሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ
›› ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
›› ትምህርት ሚኒስቴር
›› ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

መገናኛ ብዙሀን፡-
›› የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ)
›› የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
›› ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት
›› ሪፖርተር ጋዜጣ
›› ዴይሊ ሞኒተር ጋዜጣ

በጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተሰራጩ ሰነዶች፡- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ዝክረ ነገር (ToR) ፣ ባለ ሰባት ገፅ የመድረኩ አመታዊ የድርጊት መርሃግብር፣ ወጪ በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ናቸው፡፡

## የጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳዎች

- የ1ኛው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች ማቅረብና ማጽደቅ
- የመድረኩን የእስካሁን የሰራ ክንውን ሪፖርት ማዳመጥና በስራ ክንውኑ ላይ መወያየት
- የመድረኩን የተሻሻለ ዝክረ ነገር (ToR) ማቅረብና በዝክረ ነገሩ ላይ ውይይት ማድረግ

- የመድረኩን አመታዊ የድርጊት መርሃግብር ለተሳታፊዎች ማቅረብና በመርሃግብሩ ላይ መወያየት
- የመድረኩን አርማ ለጉባኤው ማቅረብና ውይይት በማድረግ አርማውን ማጽደቅ
- በጎደሉ የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምትክ ሌሎች ስራ አስፈጻሚዎችን መምረጥ
- የመድረኩን ንኡስ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ማካሄድ
- በኢፌድሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተዘጋጁ ወጪ በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ላይ ውይይት ማካሄድ ናቸው፡፡

# የጠቅላላ ጉባኤው ሂደት

አጠቃላይ ጉባኤው የተጀመረው ከጠዋቱ 3፡15 ሲሆን ይህም በአጠቃላይ ጉባኤው ላይ ይገኛሉ ተብሎ ከሚጠበቁት ተሳታፊዎች አብዛኛዎቹ ወደ ስብሰባ አዳራሹ ከደረሱ በኃላ ነው፡፡ የስብሰባው አመቻችና የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሆሌ ፎሌ ተሳታፊዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የአጠቃላይ ጉባኤውን አካሄድ በአጭሩ ካብራሩ በኃላ የእለቱ የክብር እንግዳ ጉባኤውን በይፋ መጀመር ከማብሰራቸው በፊት ተሳታፊዎች እራሳቸውንና የመጡበትን ድርጅት እንዲያስተዋውቁ ጋብዘዋል፡፡

የጉባኤው ተሳታፊዎች በሙሉ እራሳቸውን ካስተዋወቁ በኃላ፤ አቶ ሆሌ ፎሌ መድረኩን ለአቶ ነጋሽ ተክሉ የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ለቀዋል፡፡ አቶ ነጋሽ በእራሳቸውና በመድረኩ ስም ተሳታፊዎቹን ወደ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ የመጀመሪያው ጠቅላላ ጉባኤ እንኳን በደህና መጣችሁ በማለት፤ ጉባኤው አንደኛው እንደሆነና የመድረኩ መመስረቻ ጉባኤ ከስምንት ወራት በፊት በግንቦት ወር 2005 ዓ.ም መካሄዱን አስታውሰዋል፡፡ ከመስራች ጉባኤው በኃላ ይህ የመጀመሪያው መደበኛ ጉባኤ በይዘቱ ጥልቀት ያለው ውይይት የሚካሄድበትና መድረኩ በሁለት እግሩ እንዲቆም የሚያስችሉ ውሳኔዎች የሚተላለፉበት ይሆናል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡ በመቀጠልም አቶ ነጋሽ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የተከበሩ ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም ልዩ ኣማካሪ የሆኑትን አቶ ግደይ ዘርኡ ሚኒስትሩን በመወከል የጉባኤውን በይፋ መከፈት እንዲያበስሩ ወደ መድረክ ጋብዘዋቸዋል፡፡

አቶ ዘርኡ በንግግራቸው መግቢያ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የተከበሩ ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም በአስቸኳይ ስራ ምክንያት በጉባኤው ላይ ሊገኙ አለመቻላቸውን በመግለጽ ጉባኤውን ይቅርታ በመጠየቅ የሚኒስትሩን መልዕክት ለተሳታፊው በንባብ አቅርበዋል፡፡ ሚኒስትሩ በላኩት መልዕክት፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ሁኔታዎችን በመዳሰስ ቀጣይ አቅጣጫዎችን አልሞ ለሚያካሂደው ስብሰባ አድናቆታቸውን ከገለጹ በኃላ ሀገራችን በመተግበር ላይ የምትገኘውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትግበራ ለማሳካት በከፍተኛ ርብርብ ላይ ላይ እንደምትገኝ በማስታወስ ይህም ሀገሪቷን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ እንደሚያደርስና የህዝቦቻችን ተጠቃሚነት እንደሚያሳድግ እሙን ነው ብለዋል፡፡ በማያያዝም ክቡር ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው መንግስት ዘላቂ ልማት ለማምጣት ድህነት ቀናሽ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመቅረጹና በመተግበሩ ጉልህ የሆነ እድገትና ልማት መመዝገቡን ጠቁመዋል፡፡ በተመዘገቡት የልማት እመርታዎች የመንግስት የልማት አጋር የሆኑት የግሉ ዘርፍና ሲቪል ማህበረሰቡ በተለይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለልማቱ ያላቸው አወንታዊ ሚና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ብለዋል፡፡ ክቡር ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው እንደጠቆሙት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ለተቋቋመለት አላማ ስኬትና ውጤት አበክሮ እየሰራ በመሆኑ አድናቆታቸውን በመግለጽ ከዚህም በኃላ መድረኩ ደህውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ከማድረግና የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ከማሳካት አንጻር የሀገሪቱን ህጎችና ደንቦች በመከተል የሚጠበቅበት ድርሻ ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ምንም እንኳን ብዙ በጎ ተግባራት እንዳሉ ሁሉ በጎ ያልሆኑ አዝማሚያዎችን መቅረፍ መድረኩ ሊያተኩርባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መሀል አንዱ መሆኑን በመጠቆምና እነዚህና ሌሎች የመድረኩ ተልዕኮዎች ውጤታማ እንደሚሆኑ በመተማመን ጠቅላላ ጉባኤው በውል መከፈቱን አብስረዋል፡፡

# አጀንዳዎችን ማቅረብና ማጽደቅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ዋና ጸሀፊ የሆኑት አቶ ውብሸት ወ/ማርያም የጠቅላላ ጉባኤውን አጀንዳዎች (የአጀንዳዎችን ዝርዝር ከላይ ይመልከቱ) አንድ በአንድ በማብራራት ውይይት እንዲደረግበት ለተሳታፊዎች አቅርበዋል፡፡ ከአጀንዳዎችም በተጨማሪ አቶ ውብሸት እያንዳንዱን መርሃግብር ከነአስፈጻሚው አካል ጭምር በጥልቀት አቅርበዋል፡፡ ከዚያም በመቀጠል የስብሰባው አመቻች አቶ ሆሌ ፎሊ ከቀረቡት አጀንዳዎች በተጨማሪ በኢፌድሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተዘጋጁና ከዚህ ቀደም ውይይት የተካሄደባቸውን “ወጪ በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ” ላይ ከኤጀንሲው በመጡ ባለሙያዎች ማብራሪያ እንደሚሰጥባቸው ጠቁመዋል፡፡ አቶ ሆሌ ከተጠቀሱት አጀንዳዎች ውጭ ተጨማሪ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በተሳታፊዎቹ በኩል ካለ ጥያቄ አቅርበዋል፤ ሆኖም ቤቱ ምንም አይነት ጥያቄና ተጨማሪ አስተያየት በአጀንዳዎቹ ላይ ባለማቅረቡ ለውይይት የቀረቡት የጉባኤው አጀንዳዎች በሙሉ መግባባት ጸድቀዋል፡፡

## 3.1. የመድረኩ የእስካሁኑ የስራ ክንውን ሪፖርትና በስራ ክንውኑ ላይ የተደረገ ውይይት

ከምስረታው ግንቦት 2005 ዓ.ም አንስቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ያከናወናቸውን ተግባራትና ያደረጋቸውን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ያቀረቡት አቶ ነጋሽ ተክሉ የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መድረክ ሂደት በሚለው ገለጻቸው፤ አቶ ነጋሽ ይህ መድረክ ከሶስቱም ዘርፎች (የውጭ፣ የኢትዮጵያ ነዋሪዎችና ኢትዮጵያዊ) የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራት ተነሳሽነት ውጤት እንደሆነና የሚጋሯቸው ተግዳሮቶች እንዳሉ ከተገነዘቡ በኃላ የጋራ መድረክ በማቋቋም ችግሮችን መፍታት እንዳለባቸው በማመናቸው ምክንያት የተጸነሰ መድረክ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ መድረኩን በመመስረቱ ሂደት ውስጥ የቀድሞው ማለትም በCCRDA ይገኝ የነበረው ግብረ ኃይል (Task force) አመራሮች ወሳኝ ሚና መጫወታቸው የሚዘነጋ አለመሆኑን አስታውሰዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሶስቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዘርፍ ወደ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የሥራ ቡድን (CSSWG) የተወከሉት ከመንግሥታዊ ካልሆኑ ግብረ ሃይል ኮሚቴ አባላት ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ ስለ መንግሥታዊ ያልሆነው ግብረ ሃይል የስራ ዘመን መጠናቀቅና ስለ አዲሱ መድረክ አስፈላጊነት ተደጋጋሚ ውይይት ማድረጋቸውን አብራርተዋል፡፡

አቶ ነጋሽ እንዳብራሩት በኤጀንሲው መልካም ፈቃድና ከቀድሞው ግብረ ኃይል (Task force) አመራር አባሎች ረቂቅ መርሃግብር በማቅረብ በተደረጉት ጥልቅ ውይይቶች መነሻነት በግንቦት 8 ቀን 2005 ዓ.ም የመድረኩ መመስረቻ አጠቃላይ ስብሰባ መካሄዱን አስታውሰዋል፡፡ የስብሰባውን ሂደትም በተመለከተ ሁሉም ስብስቦች የተገኙበት ማለትም አሁን እዚህ ጉባኤ ላይ የሚገኙትን አካላት ጨምሮ ከየክልሉ በህብረቶች ያልታቀፉ ወኪሎችን በመምረጥ እንዲልኩ በማድረግ ምልአተ ጉባኤውን ያረጋገጠ የመመስረቻ ስብሰባ መካሄዱን አብራርተዋል፡፡

መመስረቻ ጉባኤው ላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ጥልቅ ውይይት ከተካሄደ በኃላ በተለይም አሁንም ወደዚህ ጉባኤ ዳብሮ በመጣው የመመስረቻ ህገ ደንቡ ምን ይዘት፣ ምን አላማ፣ ምን አይነት እንቅስቃሴ ይኑረን፣ ምን ብንሰራ ነው አሁን በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ያለውን ጥንካሬዎችን በማስቀጠል አሊያም ችግሮችን በማስወገድ የበለጠ የልማት አጋርነታችንን የምናረጋግጠው የሚል ሰፊ ውይይት መደረጉን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ስራውን በላቀ ደረጃ ሊመሩና ሊያስተባብሩ የሚችሉ ሰባት የተለያዩ ድርጅቶችን የሚወክሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መመረጣቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

እነኝህም፤

1. ኔትወርክ ኦፍ ኢትዮጵያን ውሜን አሶሴሽንስ (NEWA) - ወ/ሮ ሳባ ገ/መድህን
2. ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኢን ኢትዮጵያ (PANE) - አቶ አሸቱ በቀለ
3. ፖፑሌሽን ሄልዝ ኤንድ ኢንቫይሮመንት ኢትዮጵያ ኮንሶርተየም (PHE-EC) - አቶ ነጋሽ ተክሉ
4. ቮለንተሪ ሰርቪስ ኦቨርሲስ (VSO) - አቶ ውብሸት ወ/ማርያም
5. ኢትዮጵያን ናሽናል ዲሴቢሊቲ አክሽን ኔትወርክ (ENDAN) - ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ
6. ኮንሰርተየም ኦፍ ሪፕሮደክቲቭ ሄልዝ አሶሲዬሽን /CORHA/ - አቶ ሆሌ ፎሌ
7. ዩኒየን ኦፍ ቻሪቴብል ውሜን አሶሲዬሽን (UCWA) - ወ/ሮ አዜብ ቀለመወቅ

የእነዚህ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ከተካሄደ በኃላ በወቅቱ በጸደቀው መመሪያ መሰረት ለመድረኩ ስራ አስፈጻሚነት የተመረጡት አባላት ተከታታይ ውይይቶችንና ስብሰባዎችን በማድረግ መድረኩ የተጣለበትን ሃላፊነቶችና ተግባራትን ለማከናወን ያስችለው ዘንድ ከስራ አስፈጻሚዎቹ መካከል የሚከተሉት ግለሰቦች በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃዎች እንዲያገለግሉ መመረጣቸውን አስታውሰዋል፡፡

› በሊቀመንበርነት - ወ/ሮ ሳባ ገ/መድህን
› በምክትል ሊቀመንበርነት - አቶ ነጋሽ ተክሉ
› በፀሃፊነት - አቶ ውብሸት ወ/ማርያም
› በአባልነት
  › አቶ ሆሌ ፎሌ
  › አቶ አሸቱ በቀለ
  › ወ/ሮ አዜብ ቀለመወርቅ
  › ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ሲሆኑ

እንደ አቶ ነጋሽ ገለጻ ከተወሰኑ ወራት እንቅስቃሴ በኃላ የመድረኩ ሊቀመንበር የሆኑት ወ/ሮ ሳባ ገብረመድህን የከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመከታተል ረዘም ላለ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር በመሄዳቸው ምክንያት የመድረኩን ውስጠ ደንብ መሰረት በማድረግ ማለትም የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ አባላት ዳግም ምርጫ በማድረግ አቶ ነጋሽ ተክሉ በሊቀመንበርነት፣ ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ በምክትልነትና አቶ ውብሸት ወ/ማርያም በፀሐፊነት እንዲቀጥሉ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በሪፖርቱ እንደቀረበው የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- በመድረኩ የመመስረቻ ስብሰባ ላይ የቀረበውን የመመስረቻ ደንብ በማሻሻል ለአንደኛው ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቧል

- የመድረኩን አመታዊ የድርጊት መርሃግብር አዘጋጅቷል

- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም በኢፌዲሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲና ከተለያዩ ለጋሽ አካላት ጋር የምክክር መድረኮችን በመፍጠር የመድረኩን ስልጣን ሀላፊነትና ግዴታዎችንና የወደፊት አቅጣጫዎችን በሚመለከት ውይይቶችን አካሂዷል

- የመድረኩን አርማ፣ ማህተም፣ ባንክ አካውንት በማዘጋጀት፤ አርማውን ለዚህ ስብሰባ ለውሣኔ አቅርቧል

- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የመድረኩን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ አስፈላጊነትና ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት በጥልቀት ተወያይቷል፤ በቀጣዩ መደበኛ ስብሰባ ላይ ለመድረኩ ምክር ቤት ውይይት እንዲቀርብ ያደርጋል

- የCCRDA ዳይሬክተር ዶ/ር መሸሻ ሸዋረጋ በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወክሎ ከኤጀንሲ ቦርድ አካል ጋር ስብሰባዎችን በማካሄድና ይህንንም የጋራ እንቅስቃሴ በማቀናጀት አስፈላጊ መረጃዎችና የተገኙ ውጤቶች ወደ መድረኩ እንዲደርሱ ስርዓት ተበጅቷል

- ህብረቶችን በመወከል የሚሳተፉት ሌላው የቦርድ አባል የሆኑትን ዶ/ር ወልዳይ አምሃን በዚህ ስብሰባ እንዲገኙልን ጥሪ አቅርበናል

- በቀድሞ ግብረኃይል ስምና ቁጥጥር ስር የነበሩ ንብረቶች ለመድረኩ እንዲተላለፉ ከCCRDA ጋርና ከለጋሽ አካላት ጋር በመነጋገር ላይ ይገኛል። የCCRDA ዳይሬክተር ዶ/ር መሸሻ ሸዋረጋ ንብረቶቹ በእርግጥም በድርጅታቸው እጅ እንደሚገኝ አረጋግጠው CCRDA ንብረቶቹንም ለማስረከብ ያለውን ዝግጁነት ገልጸዋል። ነገር ግን ድርጅቱ ይህን ከማድረጉ በፊት የለጋሾችን በጎ ፍቃድ መጠየቅ እንዳለበትና ይህንንም በማድረግ ከለጋሾች ጋር በመነጋገር ንብረቱ ለመድረኩ የሚተላለፍበትን ስርዓት ለመዘርጋት ጥረት እየተደረገ ነው።

- ከአካል ጉዳተኞች ህብረት ጋር ስለ አጠቃላይ ሁኔታዎችና ከመድረኩ ምን አይነት ድጋፎችን እንደሚሹና የአካል ጉዳተኞች ማህበራት አባላት አስተዋጽኦ የሚጠናከርበትን መንገድ ያመላከተ ውይይት አድርጓል። ይህም ኤጀንሲው ባወጣው መመሪያ መሰረት አነኝህ ማህበራት ወደ ሀገር በቀል ባህሪያቸው መጠናከር እንዳለባቸው ከተገለጸ ጊዜ ጀምሮ እንዴት ሽግግሩን እውን ሊያደርጉት እንደሚችሉ ያለመ ነበር።

- የመድረኩን ፅ/ቤት ለማቋቋም በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

- መድረኩን ለተለያዩ የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ክልሎች ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል።

- ይህ አንደኛ መደበኛ ጉባኤ እንዲካሄድ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ከአባላት፣ ከመንግስት፣ ከክልሎች፣ ከለጋሽ ድርጅቶችና ከጋዜጠኞች ተሳታፊዎችን ጋብዟል።

- ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለCSSP በማቅረብ ድጋፍ መገኘቱና ይህንንም ጉባኤ በእነርሱ ድጋፍ ለማካሄድ በቅተናል።

- በኤጀንሲው እና በሚኒስቴር መስሪያቤቶች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በተገኙበት የጋራ መድረክ መመሪያውን ለማሻሻል ያለሙ ውይይቶች ላይ በመሳተፍ በትራንስፖርት፣ በስልጠናና አቅም ግንባታ ዙርያ መልካም የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርቧል። በተለይም የመንግስት አካላት በቀጥታ ከህብረተሰቡ ጋር የተገናኙት (Front line) የሚሰጠው ስልጠና የአላማ ማስፈፀሚያ እንዲሆን በስፋት ለማሳመን ሞክረናል።

- በቋሚ ኮሚቴው አባላት በኩል በCSSWG አባልነት በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የሚመለከቱ ጉዳዮችና ሃሳቦችን በማንሳት በቀጣይነት በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን።

አቶ ነጋሽ በሪፖርታቸው አጽንኦት ሰጥተው እንዳስቀመጡት ይህን መድረክ ከቀድሞው ግብረሀይል (Task force) የሚለየው፤ ያለፈው ግብረሀይል ይንቀሳቀስ የነበረው ከአንድ ጥምረት ጋር ብቻ በመቀናጀት መሆኑን

አስታውሰው፤ ይህ መድረክ ግን አጠቃላይ እንቅስቃሴው እውቅና አግኝቶና የራሱ የሆነ የባንክ ሂሳብ፣ ቋሚ ጽ/ቤትና እውቅና ያለው የራሱ የሆነ አርማ ያለው መሆኑ ለበለጠ ስኬት እንደሚያግዘው በዝርዝር አስረድተዋል፡ ፡ ለዚህ ዋናው ማሳያ የሚሆነው መድረኩ ይህንን ጉባኤ ለማዘጋጀት ይችል ዘንድ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለCSSP በማቅረብ በህጋዊ መንገድ ድጋፍ ማግኘት መቻሉ ነው፡፡ የመድረኩ ሊቀመንበር አቶ ነጋሽ ተክሉ አክለውም ይህ ጉባኤ እውን ይሆን ዘንድ ድጋፍ ላደረገው CSSP በእራሳቸውና በመድረኩ ስም ከፍ ያለ ምሥጋና አቅርበዋል፡፡ በመጨረሻም አቶ ነጋሽ በሪፖርቱ ውስጥ የተካተቱት ሀሳቦች መነሻ ነጥቦች መሆናቸውን በመጠቆም የጉባኤው ተሳታፊዎች በውይይት እንዲያዳብሯቸው ጠይቀዋል፡፡



አቶ ነጋሽ ተክሉ የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሪፖርት ሲያቀርቡ

በመቀጠል መድረኩን የተረከቡት የስብሰባው አመቻችና የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሆሌ ፎሌ ሲሆኑ ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ ነጋሽን በማመስገን ሲሆን አክለውም በሪፖርቱ እንደቀረበው መድረኩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ያደረገው እንቅስቃሴ አንድ በአንድ መቅረቡን ካስታወሱ በኃላ መድረኩ ከመመስረቱ በፊት የነበረው ግብረሀይል (Task force) ትልቅ ሚና እንደነበረው መጠቆሙ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ከዚያም በኃላ አቶ ሆሌ በቀረበው ሪፖርት ላይ ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች ወይም ማብራሪያ የሚፈልጉ ጉዳዮች ካሉ መድረኩን ለውይይት ክፍት አድርገዋል፡፡

የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪ አቶ እስማኤል ከአፋር ዴቨሎፕመንት አሶዬሽን ሲሆኑ ያነሷቸው ጥያቄዎች ሁለት ናቸው፤ የመጀመሪያው የኮንሶርተየምና የመድረክ ልዩነት ምንድነው የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ የመድረኩ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት እንዴት ነው የሚመረጡት አባልስ ለመሆን መመዘኛው ምንድነው የሚል ነበር፡፡

አቶ ጌቱ ሙላቱ ከኔትወርክ ኦፍ ኦርጋናይዜሽንስ ኦፍ ዘ ቪዥዋሊ ኢምፔይርድ ኤንድ ብላይንድ (NOVIB) እንደተናገሩት ከመድረኩ ምስረታ ጉባኤ በኃላ የሚያበረታቱና የሚያስመሰግኑ ስራዎች መሰራታቸውን ከሪፖርቱ መስማታቸውን ገልጸው ወደ ጥያቄዎቻቸው አምርተዋል፡፡ በጥያቄያቸውም መድረኩ ሲመሰረት ተሰጥቶት የነበረው ስያሜ መድረክ ፎር ሲቪል ሶሳይቲስ አፌይር (Forum for Civil Societies Affair) ነበር አሁን ደግሞ መድረኩ የሚጠራበት ስም ኢትዮጵያን ፌዴራል ቻሪቲስ ኤንድ ሶሳይቲስ መድረክ የሚል ነው ስለዚህ ይህ የተደረገው ለውጥ እንዴት ሊመጣ ቻለ ልዩነቱን ተከትሎ የቅርጽና የተግባር ልዩነት ያመጣ እንደሆነ ማብራሪያ ቢሰጥበት የሚል ነበር፡፡ ሌላኛው የአቶ ጌቱ ጥያቄ ደግሞ የአካል ጉዳተኞች ህብረቶችን የሚመለከት ሲሆን እንደ አቶ ጌቱ ጥያቄ ወደ አራት የሚጠጉ የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ህብረቶች ሲኖሩ ለእነዚህ ህብረቶች ምን አይነት ልዩ ድጋፍ ሊደረግ ታስቧል ወይስ ይህ ልዩ ድጋፍ የሚመለከተው በአደረጃጀት ባህሪያቸው ምክንያት ወደ ኢትዮጵያዊ ህብረትነት እንዲዞሩ የተደረጉ ሊኖሩ ይችላሉ እናም አነርሱን ብቻ የሚመለከት ነው ወይስ ሌሎቹንም ይጨምር ይሆን ወይ የሚል ነበር፡፡

ከአለም የእርቅና የሰላም ግብረሰናይ ድርጅት አቶ ጥጋቡ ሀይሌ በሰጡት አስተያየት በሪፖርቱ ላይ በአብዛኛው የተጠቀሱት የተነሳሽነትና መሰል ጉዳዮች ነበሩ ብለው፤ በመጀመሪያ የመድረኩን ራዕይ፣ ይዞ የተነሳውን አላማ ምንነት፣ ምን ጋር ነው መድረስ የሚፈልገው የሚሉት ሃሳቦች ግልጽ መሆን እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡ ፡ እንደ አቶ ጥጋቡ አስተያየት፤ መድረኩ ራዕዩን ካስቀመጠ በኃላ የግቦቹን ምንነትና የአደረጃጀቱን ቅርጽ በግልጽ ከለየ ያጠቃላይ ጉባኤው አባላት ይበልጥ ገብቶን እንድንሰራበት ያደርጉናል በማለት አስተያየታቸውን ደምድመዋል፡፡

አቶ ያእቆብ ከፕሮ ዴቨሎፕመንት ኔትወርክ፤ ይህ ጉባኤ ከመስራቹ ጉባኤ በኃላ የመጀመሪያ መድረክ መሆኑን በመጠቆም ይህ መድረክ በመፈጠሩ የተሰማቸውን ልባዊ ደስታ በመግለጽ ይህ የውይይት መድረክ እውን እንዲሆን ያደረጉትን አካላት በወከሉት ጥምረትና በመድረኩ አባላት ስም አመስግነዋል፡፡ በመጀመሪያ የመድረኩ ምስረታ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች እርሳቸውንም ጨምሮ ባለፉት ስምንት ወራት ውስጥ የነበሩ እንቅስቃሴዎች ምን ነበሩ በሚለው ላይ ብዙ ጥያቄዎች የነበራቸው መሆኑን አልሸሸጉም፡፡ ነገር ግን ዛሬ በቀረበው ሪፖርት እንደተመለከቱት ከነበረው ጊዜ አንጻር ከበቂ በላይ ስራዎች የተሰሩ መሆናቸን ለመገንዘብ መቻላቸውን ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም አቶ ያዕቆብ እንዳነሱት ከዚህ በላይም መሄድ ይቻል እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ በጥያቄያቸውም የቀድሞው ግብረሀይል (Task force) ይጠቀምባቸው የነበሩ ንብረቶችን

በተመለከተ የሰው ሀይሉንም ጭምር ይህ አዲሱ መድረክ እንዲወርስ ለማድረግ ጥረቶች እነደነበሩ ጠቁመው የሰው ሀይሉን በተመለከተ በጀት የሚፈልግ በመሆኑ እንዳልተቻለ አስታውሰው፤ ንብረቱን በተመለከተ ግን የአሁኑ መድረክ ወደ ሚንቀሳቀስበት አዲስ ቢሮ ማዛወሩ ለምን ይህን ያህል ረጅም ጊዜ ወሰደ በማለት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም አቶ ያእቆብ ያነሱት ሁለተኛው ጥያቄ የቀድሞው ግብረሀይል "ታስክ ፎርስ ፎር ኢኔብሊንግ ኢንቫይሮመንት" በሚል ርዕስ ይካሄዱ የነበሩ የጥናት ውጤቶችንና በሲቪክ ማህበራት ላይ ያተኮሩ ከተለያዩ አካላት ጋር ይካሄዱ የነበሩ የውይይት ወጤቶችን ወስዶ ለአሁኑ የመድረኩ እቅስቃሴ እንደ ግብአትነት ለመጠቀም ያልተቻለበት ምክንያት ግልጽ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡

ከተሳታፊዎች ለቀረቡት ጥያቄዎች በመጀመሪያ ምላሽ የሰጡት የመድረኩ ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ ነጋሽ ተክሉ ሲሆኑ እንደ እርሳቸው ገለጻ በአቶ እስማኤል እና በአቶ ጥጋቡ ለቀረቡት ጥያቄዎች በወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ የሚቀርበው የመድረኩ ዝክረ ነገር (ToR) በቂ ምላሽ እንደሚሰጥ ጠቁመዋል፡፡ እንደ አቶ ነጋሽ አገላለጽ የጉባኤው ዋና አጀንዳና በትኩረት ከሚወያይባቸው ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ ይህ ዝክረ ነገር መሆኑን በመጠቆም ሰነዱ የመድረኩን አላማ፣ አደረጃጀቱን፣ አንማን ናቸው አባለቱ የሚሉትን ወሳኝ ጥያቄዎች የሚመልስ ይሆናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ይህ ስብስብ ግቡ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን እስከ ሶስት ሺህ የሚሆኑ ማለትም በውጭ፣ በኢትዮጵያ ነዋሪዎችና ኢትዮጵያዊ በሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሁሉን አቀፍ በሆነና በተደራጀ መልኩ በውክልናቸው ያቋቋሙት መድረክ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ማንኛውም በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ህብረቶች የመድረኩ አካል መሆን እንደሚችሉ ጠቁመው፤ ነገር ግን በህብረትነት ያልታቀፉ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ደግሞ እራሳቸውን አደራጅተው በውክልና በመድረኩ ላይ መሳተፍ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡ አቶ ነጋሽ አጽንኦት ሰጥተው እንዳሳሰቡት ይህ መድረክ የጥምረቶች ጥምረት አለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት እንደሚገባና ይህ ስብስብ መድረክ እንደመሆኑ መጠን በህብረት ያልታቀፉትም በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በውክልና ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል መመቻቸቱን አስታውሰዋል፡፡ የVSO ተሳትፎና የአሰፈፃሚው ኮሚቴው አባል መሆንም ከዚህ አንፃር እንደሆነ እነደምሳሌ ገልፀዋል፡፡

አቶ ጌቱ ያነሱትን ጥያቄ በሚመለከት አቶ ነጋሽ መድረኩ በቅርበት ውይይት ያደረገው በአደረጃጀት ባህሪያቸው ምክንያት ወደ ኢትዮጵያዊ ህብረትነት እንዲያዘነብሉ የሚፈለጉ ህብረቶችን የሚመለከት ሲሆን፣ መድረኩም በምን መልኩ ይህንን ሂደት መደገፍ እንደሚቻል ከእነኝህ ህብረቶች ጋር በቢሮዋቸው በመገኘት ጥልቀት ያለው ውይይቶችን ማካሄዱን ገልጸዋል፡፡ ሌላው በአቶ ጌቱ የተነሳው ስያሜን የተመለከተ ጥያቄ ሲመልሱ አቶ ነጋሽ እንደጠቆሙት ፎረም ፎር ሲቪል ሶሳይቲስ አፌይር (Forum for civil societies Affair) የሚለው ስያሜ በምንም መልኩ የዚህ መድረክ ስያሜ ሆኖ እንደማያውቅ "ሲቪክ ማህበረሰብ" የሚለው ስያሜ ይህንን መድረክ እንደማይወክልና በመድረኩ መመስረቻ ጉባኤ ላይም ውይይት እንደተደረገበት አስታውሰዋል፡ ፡ ይህም የሆነበት ምክንያት "ሲቪክ ማህበረሰብ" ከተባለ ፖለቲካዊ አደረጃጀቶችንም የሚጨምር በመሆኑ ነው፡፡ ይህ መድረክ ደግሞ ዋነኛ ሚናው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን መደገፍ እንደመሆኑ መጠን በአሁኑ ወቅት ያለው የመድረኩ ስያሜ (የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ) "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ከመጨመሩ በስተቀር ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረው መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በአቶ ያዕቆብ ከቀረበው ጥያቄ ጋር ተያይዞ ማለትም በቀድሞው ግብረሃይል እጅ የሚገኙትን ንብረቶችን ወደ መድረኩ ማስተላለፍና ግብረሃይሉ የጀመራቸውን ስራዎች ከማስቀጠል አንጻር ብዙ ጥረቶች ተደርገው የነበረና አሁንም መድረኩ በከፍተኛ ጥረት ላይ እንደሚገኝ ተጠቅሷል፡፡ አቶ ነጋሽ እንደገለጹት መድረኩ እንቅስቃሴ በጀመረባቸው የመጀመሪያ ወራት የቀድሞውን ግብረሃይል ሰራተኞች ወደ መድረኩ ለማሸጋገር ጥረት ተጀምሮ እንደነበረና ሰራተኞቹ ተጠያቂነታቸውና ሀላፊነታቸው ለCCRDA መሆኑን በመግለጻቸው ዝውውሩ አለመሳካቱን ተናግረዋል፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ከቀድሞ አመራሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶችን በማድረግ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸውን አቋም ለማወቅ ጥረት መደረጉን ገልጸው ከዚህም በተጨማሪ መድረኩ ለCCRDA ደብበዳቤ መጻፉንና የተወሰኑትን ንብረቶች በማስተላለፍ ረገድ በቃል ደረጃ በጎ ምላሾችም መገኘታቸውን አብስረዋል፡፡ ስለዚህም መድረኩ ይህንን ሂደት ከማሳካት አንጻር የገጠመው የአፈጻጸም ችግር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም መድረኩ በአሁኑ ወቅት ለቀድሞው ግብረሃይል ድጋፍ ያደርጉ የነበሩ ለጋሽ አካለትን ይሁንታ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝና በዚህም ምክንያት የግብረሀይሉን ንብረቶች CCRDA ሊያስረክብ አለመቻሉን ገልጸው ከለጋሾቹ አንዱ ከሆነው Irish Aid በኩል ግን ይሁንታ መገኘቱን ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡ አጋጣሚውንም በመጠቀም አቶ ነጋሽ በመድረኩ ስም ሌሎች ለጋሾችም ይህንን ሂደት እንዲያፋጥኑ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

በሁለተኛው ዙር የአስተያየትና ጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ የመጀመሪያው አስተያየት ሰጪና ጥያቄ አቅራቢ ወ/ሮ ብዙወርቅ ከIrish Aid ሲሆኑ በአስተያየታቸው ከCCRDA ወደ መድረኩ የሚተላለፉ ንብረቶችን በተመለከተ የድርጅታቸውን አቋም አብራርተዋል፡፡ ወ/ሮ ብዙወርቅ እንደገለጹት Irish Aid ንብረቶቹን መድረኩ ተረክቦ ቢጠቀምባቸው ድርጅታቸው ፍቃደኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም Irish Aid ከፈቃደኝነቱም ባሻገር አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ጠይቆ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ይህም አንደኛ CCRDA ስለ ንብረቶቹ አይነትና ምንነት ለIrish Aid እንዲያሳውቅ፤ ሁለተኛ ንብረት ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት በሚተላለፍበት ወቅት መመሪያ እንዳለው ይታወቃል፤ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ CCRDA እንዴት በመመሪያው መሰረት የሚጠበቅበትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላቱን ወይም ከዚህ ሃላፊነት ነጻ የሚሆን

(exempted) ከሆነ ይህንን የሚያሳይ ሰነድ እንዲያቀርብ መጠየቁን አስታውሰዋል፡፡ ከመድረኩ በኩል በወ/ሮ ብዙወርቅ አስተያየት ላይ ተጨማሪ ሃሳብ የሰጡት አቶ ነጋሽ ተክሉ ከIrish Aid እና ሌሎች ለጋሾች በኩል ለCCRDA የቀረቡት ማብራሪያዎች ተገቢ መሆናቸውን አረጋግጠው የመድረኩም ፍላጎት መሆኑን አስምረውበታል፡፡ በመጨረሻም አቶ ነጋሽ በአሁኑ ወቅት ንብረቶችን ለማስተላለፍ እየተደረገ ያለውን ጥረት አድንቀው፣ በIrish Aid እና በሌሎች ለጋሾች በኩል ይህ ስራ የሚፋጠንበትን መንገድ እንዲፈልጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ ውይይት በኃላ የጉባኤው ተሳታፊ በሻይ እረፍት ፋታ ለመውሰድ የመሰብሰብያ አዳራሹን ለቆ ወጥቷል፡፡



ወ/ሮ ብዙወርቅ ከተተ ከIrish Aid አስተያየት ሲሰጡና ጥያቄ ሲያቀርቡ

## 3.2. በተሻሻለው የመድረኩ ዝክረ-ነገር (ToR) ላይ የቀረበ ማብራሪያና በዝክረ-ነገሩ ላይ የተደረገ ውይይት

የጉባኤው ተሳታፊ በቀጥታ ከሻይ እረፍት እንደተመለሰ የቀጠለው መርሀግብር በመድረኩ ምክትል ሊቀመንበር ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ አማካኝነት የተሻሻለው የመድረኩ ዝክረ-ነገር (ToR) ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ከመሆኑም ባሻገር ገንቢ አስተያየቶች ተሰጥተውበታል (አባሪ አንድን ይመልከቱ)፡፡

ወ/ሮ የትነበረሽ በገለጻቸው ላይ እንደጠቆሙት ዝክረ-ነገሩ በአጠቃላይ ስለ መድረኩ አላማ፣ ተልዕኮ፣ አወቃቀሩንና የህላፊነት ወሰኑን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ዝክረ ነገሩ 23 አንቀጾች ሲኖሩት በውስጡ ከተካቱት አንኳር ርዕሰ ጉዳዮች መካከል፣ ስለ ስያሜው፣ አመሰራረቱና የተመሰረተበትን አላማና ተግባራት፣ በመድረኩ አባል መሆን ስለሚችሉ አካላት መብትና ግዴታዎች፣ የአጠቃላይ ጉባኤውንና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ስልጣንና ተግባራት የሚወስኑ አንቀጾች ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም እንደ ወ/ሮ የትነበርሽ ገለጻ ዝክረ-ነገሩ በመድረኩ ውስጥ የሚገኙ ንኡሳን ኮሚቴዎችን የስራ ድርሻዎችንና ድርጅታዊ መዋቅር የሚያሳይ ከመሆኑም ባሻገር የመድረኩን ጸሀፊ፣ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ስልጣንና ተግባራት የሚደነግግ ነው ብለዋል፡፡ ከዚህም ባለፈ ሰነዱ ስለ ኦዲትና የፋይናንስ አስተዳደር ጉዳዮችና በሰነዱ ላይ ማሻሻያ ስለሚደረግበትም መንገድ ይደነግጋል ብለዋል፡፡

ከህብረቶች በተለየ መልኩ ይህን መድረክ ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል ዋነኛው ሶስቱንም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ዘርፍ (የውጭ ሀገር፣ የኢትዮጵያ ነዋሪዎችንና ኢትዮጵያዊያንን) የሚወክልና በአንድ ላይ የሚያገናኝ እንደመሆኑ መጠን ይህ መድረክ ችግሮቻችንን የምንቀርፍበት፣ ጥንካሬዎቻችንን የምናጎላበትና በትብብር የምንሰራበት ነው በማለት የመደረኩን ጠቀሜታ አመላክተዋል፡፡ ሌላው ምክትል ሊቀመንበሯ አስምረውበት ያለፉት ጉዳይ ቢኖር፣ መድረኩ ካሉት አላማዎችና ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንጻር ህብረቶች የተሰማሩባቸውንና እያካሄዷቸው ያሉትን ስራዎች ላለመድገም ተደጋገፎ በተቀናጀ መንገድ ለመስራት ጥረት



ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ToR ለጉባኤው ሲያቀርቡ

መደረጉንና እንደሚደረግም አስታውቀዋል፡፡ በወቅቱ እንደተገለጸውም መድረኩ ሶስት ንኡሳን ኮሚቴዎች እንዳሉት አነኝህም ምርምርና ውይይት (Sub-Comitee for Research and Dialogue)፣ ማስተዋወቅና ተጠያቂነት (Sub-Comitee for Promotion and Accountablity) እና አጋርነትና በትብብር መስራት (Sub-Comitee for Partnership and Collaborative Engagement) የሚሉት መሆናቸው ተገልጿል፡፡

በመቀጠል የጉባኤው አመቻች የሆኑት አቶ ሆሌ አቅራቢዋን በማመስገን መድረኩን ለጥያቄዎች፣ ለተጨማሪ ግብአቶችና ውይይት ክፍት አድርገዋል፡፡

አቶ ኤፍሬም ብርሃኑ ከኮንሶርትየም ኦፍ ዩዝ ዴቨሎፐመንት ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኢትዮጵያ (CoYDoE) በሰጡት አስተያየት፣ በአንቀጽ 4 ላይ የተዘረዘሩት የመድረኩ ተግባራትና ኃላፊነቶች እጅግ ብዙ መሆናቸውን ጠቁመውል፡፡ አቶ ኤፍሬም በምሳሌ እንዳስቀመጡትም ቁጥር 1 የ4ኛው ማስፈጸሚያ ነው የሚመስለው ስለዚህ እነዚህ ሁለት ተግባራት ቢዋሀዱ የሚል ሀሳብ አቅርበው፣ ከዚህም በሻገር በተራ ቁጥር 3 እና 6 ላይ የተዘረዘሩት ተግባራት መድረኩ ሊያተኩርባቸው የሚገቡ የስራ ድርሻዎች ሊሆኑ እንደማይገቡ አስገንዝበዋል፡ ፡ እንደ አቶ ኤፍሬም አገላለጽ አንቀጽ 8 ላይ የተመለከተው የመድረኩ ድርጅታዊ መዋቅር ላይ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እንዴት ለንኡስ ኮሚቴው ተጠሪ ሊሆን እንደሚችል ጠይቀዋል፡፡ በተጨማሪም ለንኡስ ኮሚቴው የተሰጡት ኃላፊነቶች በሙሉ መድረኩ የሚያከናውናቸው ሲሆኑ እንደዚህ ያሉ ንኡስ ኮሚቴዎች ይህንን መሰል ሃላፊነቶችን በተደራጀ መልኩ ለመተግበር ሊቸገሩ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከኢትዮጵያ መካኒካል መሀንዲሶች ማህበር ክርስቲን የተባሉ ተሳታፊ እንደጠቆሙት የመድረኩ ዝክረ-ነገር (ToR) ሙሉ ትኩረቱን ያደረገው በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ብቻ ነው በማለት እንደሚታወቀው የሙያ ማህበራት ለሀገር ልማት የሚደርጉት አስተዋጽኦ መዘንጋት እንደሌለበት ጠቁመዋል፡፡ አንቀጽ 20 ላይ የቀረበው ኦዲትና የፋይናንስ አስተዳደር ጉዳዮችን በሚመለከተው ክፍል ውስጥ ተራ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው ክፍያዎች በመድረኩ አስተባባሪ ይፈጸማሉ የሚለው አንቀጽ በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴና በጽ/ቤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው? ወይስ ጽ/ቤቱ እራሱን ችሎ ነው ሀላፊነቱን የሚወጣው በማለት ይህ ሁኔታ እንዲብራራላቸው ጠይቀዋል፡፡

አቶ ያዕቆብ አንሙት ከፐሮ ዴቨሎፐመንት ኔትወርክ (PDN) እንደጠቆሙት የመድረኩ ስራ በዝቷል የተባለውን አስተያየት እንደማይስማሙበት ገልጸው በአንቀጽ 4 ቁጥር 2 ላይ የተቀመጠው የልምድ ልውውጥን የሚመለከቱ ተግባራት መልካም ተሞክሮዎች በመድረኩ አባል በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዘንድ እንዲታወቁ የሚሰራጩበት መንገድ መፈለግ ይኖርበታል ብለዋል፡፡ ሌላው የተጠቆመው በአንቀጽ 4 ቁጥር 1 እና 4 ይዋሀዱ ተብሎ በሌላ ተሳታፊ የተሰጠውን አስተያየት እንደማይስማሙበት በመጠቆም የተዘረዘሩት የመድረኩ ተግባራትና ኃላፊነቶች ተገቢ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ሌላው አንቀጽ 5 ላይ የቀረበው አባልነትን የሚመለከት ሲሆን እንደ አቶ ያዕቆብ አስተያየት ምንም እንኳን አባልነት በፈቃደኝነት ቢሆንም እያንዳንዱ ህብረት ላይ የሚጣሉ ገዴታዎችና ሀላፊነቶች ቢኖሩ መልካም ነው ካሉ በኃላ በመድረኩ የተለያዩ አካላት ላይ ያሉ የተጠያቂነት ወሰንን የተመለከቱ ጉዳዮች በግልጽ መቀመጥ ይኖርባቸዋል በማለት አጠቃለዋል፡፡



አቶ ያዕቆብ አንሙት ከፐሮ ዴቨሎፐመንት ኔትወርክ (PDN) አስተያየት ሲሰጡ

አቶ ወንዱ ከኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ማህበራት ህብረት (CENCEDA) የመድረኩን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን በበጎ ፈቃደኝነት ይህንን ሁሉ ተግባራት ማከናወናቸውን አድንቀው፣ ይህ ዝክረ-ነገር (ToR) ተብሎ የቀረበው ሰነድ የመተዳደሪያ ደንብ፣ የመመስረቻ ጽሁፍ፣ የመግባቢያ ሰነድ ወይም ሌላ መሰል ስያሜ ሊሰጠው እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

አቶ ብዛየነህ ገ/እግዚአብሄር ከኢፌዴሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የወ/ሮ የትነበርሽን አቀራረብ አድንቀው እርሳቸውም በአቶ ወንዱ የተነሳው በዝክረ-ነገሩ (ToR) ስያሜ ላይ ያተኮረውን ጥያቄ እርሳቸውም እንደሚጋሩት ጠቁመው ይህ ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ ቢሆን ጠቃሚ ይሆናል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 5 ላይ የቀረበው አባል ስለሚሆንበት ሁኔታ፣ የአባልነት መመዘኛዎችና የስራው ወሰን በግልጽ መቀመጥ ይኖርታል ሲሉ አስተያየታቸውን ለግሰዋል፡፡ በመጨረሻም እንደ አቶ ብዛየነህ አስተያየት መድረኩ በሚፈርስበት

ጊዜ ንብረቶቹ በምን መልኩ እንደሚተላለፉ፣ የግልግልና ግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓትና የመድረኩ የገቢ ምንጭ ሰነዱ ላይ መካተት ይኖርበታል በማለት ተናግረዋል፡፡



አቶ ወንዱ በቀለ ከኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ማህበራት ህብረት ToR ላይ አስተያየት ሲሰጡ

ለተነሱት ጥያቄዎችና አስተያየቶች በመጀመሪያ ምላሽ የሰጡት ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ሲሆኑ፤ እንደ እርሳቸው አባባል ይህ ሰነድ ምን ተብሎ ይጠራ በሚለው ላይ ኮሚቴው "መመስረቻ ሰነድ" በሚለው ላይ ስምምነት ላይ መድረሱን ጠቁመው፤ አሊያም በቤቱ ውሳኔ ሰጥቶበት ተሻሽሎ የሚቀጥልበት መንገድ እንደሚፈለግ ጠቁመዋል፡፡ አቶ ኤፍሬም ያነሱትን በአንቀፅ 4 ቁጥር 3 እና 6ን የተመለከተውን ጥያቄ በሚመለከት፤ የመረጃ ልውውጥን ተግባር የሚያከናውን አካል የለም ስለዚህ ይህ መድረክ የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት እንደ ድልድይ ሆኖ እንዲያገለግል እንደሚፈለግም ጨምረው ገልጸዋል፡፡ ስለዚህም አንቀጽ 4 ቁጥር 6 ላይ የተቀመጡ የቃላት አጠቃቀሞችና አንዳንድ የቃላት አገባቦች ላይ ማሻሻያዎች እንደሚደረጉና የተዘረዘሩት ተግባራት ባሉበት እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል፡፡ አያይዘውም ንኡሳን ኮሚቴዎች ብዙ የስራ ድርሻ እንዳሉዋቸው አምነው፤ መድረኩ እነዚህ ንኡሳን ኮሚቴዎቹ በሂደት የሚጠናከሩበት መንገድ መፍጠር እንደሚቻል አስገንዝበዋል፡፡ የክፍያ አፈጻጸምንና የተጠያቂነት ወሰንን በተመለከተ የሴክረቴሪያቱን አስተባባሪ ስልጣንና ተግባር የሚመለከቱ ዝርዝር እንቀጾች እንደሚጨመሩ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩልም ወ/ሮ የትነበርሽ የማህበራት ተሳትፎን በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄ ሲመልሱ፤ መድረኩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ተሳትፎ በጋራ የያዘና ለአንድ አላማ የቆመ ስብስብ እንደመሆኑ መጠን ሌላ የፉክክርና የውድድር መንፈስ እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ ስለዚህም በመድረኩ ውስጥ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እኩል ማህበራትም በህብረቶቻቸው አማካኝነት እኩል ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህም በኃላ መድረኩ ለሁለተኛ ዙር ጥያቄ፣ አስተያየትና ውይይት ክፍት ተደርጓል፡፡

በመጀመሪያው ዙር በተሰጡት አስተያየቶችና በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ሀሳባቸውን ያንጸባረቁት በኢፌዲሪ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ መሰረት ገብረማርያም ሲሆኑ፤ እንደእርሳቸው አባባል መድረኩ በህግ እውቅና ያልተሰጠው ነገር ግን በኢፌዲሪ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ልዩ አስተዳደራዊ እውቅና ያገኘ መሆኑን አስታውሰው የመፍረስና የንብረት ጉዳይ በዚህ መድረክ ህልውና ላይ ሊነሳ እንደማይገባ አሳስበዋል፡፡ ጨምረውም ይህ መድረክ ማህበር ወይም ህብረት ስላይደለ የገቢ ምንጭና ሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች መነሳት የለባቸውም ብለዋል፤ አያይዘውም መድረኩ በሁለት መንገድ ሊፈርስ እንደሚችል ጠቁመው አንደኛው መድረኩ ከራሱ በኩል በአባላቱ አነሳሽነት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ አስተዳደራዊ እውቅና የሰጠው አካል ሊያፈርሰው እንደሚችል አስታውቀዋል፡፡ ይህም በመሆኑ ምክንያት መድረኩ ሊኖረው የሚችለው የማቋቋሚያ ሰነድ ሲሆን ይህ ሰነድ መድረኩ የሚመራበትም ጭምር መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በመጨረሻም አንቀጽ 4 ቁጥር 6 ላይ ላይ የተቀመጠው የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር የሚለው የስራ ድርሻ የተጀመረውንም መልካም ተሞክሮ ማስቀጠልንም ሊጨምር እንደሚገባ አበክረው ገልጸዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ በላይ ከኦቪሲ ኔትወርክ ኢትዮጵያ ያነሱት ጥያቄ የሚያተኩረው የመድረኩ መደበኛ ጉባኤ ላይ ሲሆን፤ እንደ እርሳቸው አባባል የመድረኩ ጉባኤ በአመት ለሁለት ጊዜያት መሆኑ ከወጪ አንጻር ይቻላል ወይ የሚል ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች መልካም ተሞክሮዎችንና መረጃ ልውውጥን በተመለከተ ከዚህ በፊት በቀድሞው ግብረ ሀይል የተሰሩ ስራዎችንም የዚህ እንቅስቃሴ አካል ማድረግ ቢቻል የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

አቶ አለማሁ ዲሮ ከኔትወርክ ኦፍ ኢትዮጵያን ሲቪል ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኦሮሚያ እንዳሳወቁት መድረክ የሚለው አደረጃጀት ወደፊት እያደገ የሚመጣና ግዴታና ሀላፊነትን በተመለከተ የውክልና ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ አለመሆኑን ጠቁመው፤ ያለበለዚያ ከመድረክ የተለየ አደረጃጀት ሊመጣ ነው ማለት ነው ብለዋል፡፡ አቶ አለማየሁ አክለውም መድረክ በአባል ድርጅቶችና ማህበራት የሚቋቋም እንደመሆኑ መጠን የስራ ድግግሞሽ መኖሩ አይቀሬ ነው ብለው ይህ የስራ ድርሻ በሂደት እያደገ የሚመጣበት መንገድ ቢኖር በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

ከአውሮፓ ህብረት የመጡት አቶ አካለወልድ ባንቲርጉ እንደጠቆሙት በዝክረ-ነገሩ (ToR) አንቀጽ 6

ላይ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የህብረቶች ስራ እንደሚመስሉና እነዚህ ስራዎች መደገም የሌለባቸው መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በተጨማሪም ንኡሳን ኮሚቴዎቹ ድግግሞሽ እንዳለውና የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጊዜ ውስዶ ቢመረምረው መልካም ነው ብለዋል፡፡

ወ/ሮ ብዙወርቅ ከIrish Aid የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የስነምግባር መመሪያንና የመረጃ ቋትን በሚመለከት በሰጡት ሀሳብ በ1997/98 ዓ.ም በቀድሞው ግብረ ሀይል የተሰሩ ብዙ ስራዎች መኖራቸውን አስታውሰው፤ ይህም መድረክ በወቅቱ በተሰሩት ስራዎች ላይ ተንተርሶ ስራውን ቢያስቀጥል መልካም ነው ብለዋል፡፡ ወ/ሮ ብዙወርቅ ስለ መድረኩ ስያሜ መግባባት ያለ አይመስልም በማለት በመድረኩ ማንነት ላይ ጥርት ያለ ስምምነት ሊኖር እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው አሳስበዋል፡፡ ሌላው መድረኩ ምቹ የስራ ሁኔታ እንዲኖር ይሰራ ስንል መድረኩ አድቮኬሲ ላይ ይሰራል ማለታችን ነው ወይ በማለት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡

ከዚህም በኃላ በቤቱ በቀረቡት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ላይ ከመድረኩ ሀሳብ ተሰጥቶበታል፡፡ እንደ አቶ ሆሌ ፎሌ አባባል መድረኩ አንዳንዶቹን አስተያየቶች ወዲያው እንደሚወስድ ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም የመድረኩ ሊቀመንበር አቶ ነጋሽ ተክሉ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለብዙ አመታት በሀገሪቱ ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ያለ ቢሆንም ሁሉንም ዘርፎች ያካተተ እውነተኛ መድረክ ያገኙት በአሁኑ ወቅት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ስለዘህም ይህንን መልካም አጋጣሚ ልንጠቀምበት ይገባል ብለዋል፤ አክለውም ኤጀንሲው ይህንን መሰል አስተዳደራዊ እውቅና ለመድረኩ መስጠቱን አድንቀዋል፡፡ ስለዚህም እውቅና እከተሰጠን ድረስ ማለትም የባንክ ሂሳብ መክፈት፣ ገቢ ማሰባሰብ እስከቻልን ድረስ ይህንን ሌሎች ለጋሾች ጋር ለሚኖረን አጋርነትና ትብብር ልንጠቀምበት ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡ በተጨማሪም አሁን ዝክረ-ነገር (ToR) ተብሎ የቀረበው ሰነድ "የመግባቢያ ሰነድ" ተብሎ ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል ብለዋል፡፡

እንደ የመድረኩ ምክትል ሊቀመንበር ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ ገለጻ፤ መድረኩ ተዋጽኦ ላይ ውክልናን ማስጠበቁ ምንም አይነት ችግር እንደሌለው አስገንዝበዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ወ/ሮ ብዙወርቅ ንኡሳን ኮሚቴዎችን አስመልክቶ ያነሱትን ጥያቄ በሚመለከት በሰጡት ምላሽ፤ አካሄዶችን በሂደት እያየን በማዳበር ክፍተቶችን እየሞላን እንሄዳለን ብለዋል፡፡

የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የተከበሩ ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም ልዩ አማካሪ አቶ ግደይ ዘርኡ እንደጠቆሙት፤ እንደ ህዝባዊ ፖሊሲ ትንታኔ ባለሙያነታቸው በተለይም በአውሮፓ በዋናነት የጀርመንን ልምድ ጠቅሰው ይህን መሰል መድረኮች የሚተዳደሩት በመምሪያ (Guideline) መሆኑን ጠቁመው ይህም ሰነድ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ መመሪያ ተብሎ ቢጠራ በማለት ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

አቶ ጌቱ ሙላቱ ከኔትወርክ ኦፍ ኦርጋናይዜሽንስ ኦፍ ዘ ቪዥዋሊ ኢምፔይርድ ኤንድ ብላይንድ (NOVIB) ዝክረ-ነገሩ (ToR) ቀድሞ ቢላክ ኖሮ መልካም ነበር ብለው፤ ሰነዱ በሚታይበት ጊዜ መድረኩ ከአስተዳደራዊ እውቅና በላይ የተሰጠው እንደሚመስል ገልጸው የሚዘጋጀው ሰነድ ይህንን እውቅና መሰረት ያደረገ ይሁን የሚል ሀሳብ ሰጥተው፤ ስያሜውንም በተመለከተ ቤቱ ድምጽ ሰጥቶ መጽደቅ ያለበት ብቻ ሳይሆን የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተገቢውን የህግ ባለሞያዎች አማክሮ ለቦርዱ ጉባኤ ቢያቀርብ የተሻለ ይሆናል በማለት አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

በመጨረሻም ቤቱ ባለሙያ በማማከር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የመድረኩን መተዳደሪያና መመስረቻ ሰነድ ስያሜ ለአጠቃላይ ጉባኤው እንዲያቀርብ በሙሉ ድምፅ በመወሰን በዚህ አጀንዳ ላይ የተደረገው ውይይት ተቋጭቷል፡፡

ከዚህ ውይይት በኃላ የጠዋቱ መርሃግብር በመጠናቀቁ የጉባኤው ተሳታፊ ለምሳ የመሰብሰቢያ አዳራሹን ለቆ ወጥቷል፡፡

## 3.3. በመድረኩ የ2014 ድርጊት መርሀግብር ላይ የቀረበ ማብራሪያና በድርጊት መርሀግብሩ ላይ የተደረገ ውይይት

የመድረኩ ጸሀፊ የሆኑት አቶ ውብሸት ወ/ማርያም የመድረኩ አመታዊ የድርጊት መርሀግብር ላይ ሰፊ ገለጻ ሰጥተዋል (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)፡፡ እንደ አቶ ውብሸት አገላለጽ የመድረኩ የ2014 ድርጊት መርሃግብር በአራት አበይት ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ የተከፋፈለ ሲሆን፤ እነዚህም 1ኛ የሴክተሩና የመድረኩን ተቋማዊና አስተዳደራዊ ማዕቀፍ የሚመለከቱ ስራዎችን ማዘጋጀትና ማጠናቀቅ 2ኛ የሴክተሩና የመድረኩን ማስተዋወቅ፣ ተጠያቂነት፣ አጋርነትና በትብብር መስራት 3ኛ ምርምር፣ ገንቢ ውይይቶች ማካሄድና ውክልና የሚሉት ናቸው፡፡ የድርጊት መርሃግብሩ ተግባራትን፣ የጊዜ ማዕቀፉን፣ አስፈጻሚውን አካል፣ የሚፈጸምበትን ጊዜ፣ የሚያስፈልገውን በጀት ግምትና ሊገጥሙት የሚችሉትን እንቅፋቶች ጭምር ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው ብለዋል፡፡



አቶ ውብሸት ወ/ማርያም የመድረኩ አመታዊ የድርጊት መርሀግብር ሲያቀርቡ

ከዚህም በኃላ የጉባኤው አመቻች አቶ ሆሌ ፎሌ እቅዱ በዝርዝር መቅረቡን ጠቁመው፤ የድርጊት መርሀግብሩ የመድረኩ ዝክረ ነገርና ሊያሰባስበው የሚችለውን የገንዘብ መጠን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ በተጨማሪም የመድረኩ የድርጊት መርሃግብር ውስጥ አስፈጻሚ አካላቶች ሲኖሩ እነዚህ ግለሰቦች ሃላፊነታቸውን የሚወጡት ብቻቸውን ሳይሆን ከአጠቃላይ የመድረኩ አባላት ጋር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡
በመቀጠል አቶ ሆሌ መድረኩን ለጥያቄዎች፣ ለተጨማሪ ግብአቶችና ውይይት ክፍት አድርገዋል፡፡

አቶ ጥጋቡ ሀይሌ ከአለም የእርቅና የሰላም ግብረሰናይ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ በመጀመሪያ መድረኩ ያለውን ራዕይ ማስቀመጥና ተግባራቱን በተቀመጠው ራዕይ መሰረት መመዘን ይኖርብናል ብለዋል፡፡ አቶ ጥጋቡ ጨምረውም ይህንን የድርጊት መርሃግብርም መመዘን የሚኖርብን ቀድመን ባስቀመጥነው ራዕይ መሰረት መሆን ይኖርበታል ብለዋል፡፡

አቶ ይፍክር ተፈራ ከሙያ ደህንነትና ጤና አጠባበቅ ባለሞያዎች ማህበር (OSHPA-E) የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የድርጊት መርሀግብር ማዘጋጀታቸውና በዚች አጭር ጊዜ ለውይይት ማብቃታቸውን አድንቀው፤ ሆኖም ግን በድርጊት መርሃግብሩ ውስጥ የተካተቱት ተግባራት እጅግ በዝተዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ አክለውም በአቶ ጥጋቡ የተጠቀሱት የመድረኩ ተልእኮ፣ ራዕይና ሌሎች የመድረኩን እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ አጠቃላይ ሁኔታዎች የመድረኩ እስትራቴጂክ እቅዶች ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ስለዚህ እትራቴጂክ እቅዱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ግን መድረኩ የድርጊት መርሀግብር አይኖረውም ማለት አይደለም እንደውም ጎን ለጎን መድረኩን የማስተዋወቅና ከአባሎች፣ ከባለድርሻ አካላትና ከመንግስት ጋር ተያያዥ ስራዎችን መስራት መጀመር ይኖርብናል ብለዋል፡፡

ወ/ሮ ብዙወርቅ ከIrish Aid ሁለት ጥያቄችን ያነሱ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ጥያቄ የድርጊት መርሃግብሩ ይዘት ተከታታይነት ያለው ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመው እንደ አስረጅነት ያቀረቡትም በገጽ 4 ቁጥር 2 ላይ የተቀመጠው የፌዴራል በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክን በሁሉም ክልሎች የማስተዋወቅ ስራና የምክክር ኮንፍረንሶችን ማዘጋጀት የሚለው ተግባር መድረኩ ለሚያካሂዳቸው ሌሎች ስራዎች ጠቃሚ እንደመሆኑ መጠን ቀድሞ ሊከናወን የሚገባ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በተጨማሪም የስነምግባር መመሪያው በሚዘጋጅበት ወቅት የመድረኩን እና የአባላቱን (ህብረቶቹን) ሚና መለየትና በቀድሞው ግብረሃይል (Task force) የተዘጋጁ የስነምግባር መመሪያዎችን መመልከቱም ጠቀሜታ ይኖረዋል በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት የተከበሩ አቶ መሰረት ገብረማርያም የስነምግባር ደንብን የማስፈጸም ክፍተት አለ የተባለውን ጠቅሰው፤ በቀድሞው ግብረሃይል የተዘጋጀውን የስነምግባር ደንብ መመልከታቸውንና መድረኩ ደንቡን ብቻውን ሊያስፈጽም እንደማይችል አብራርተዋል፡፡ እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ጥቆማ የስነምግባር ደንቡን የማስፈጸምና መሬት ላይ እንዲወርድ የማድረግ ስራ በህብረቶች ዘንድ የሚከወን ሆኖ፤ የህብረቶች አባል የሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ይህንን ደንብ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ በመጨረሻም የተከበሩ አቶ መሰረት እንደገለጹት

ይህ የስነምግባር መመሪያ በራሱ አስገዳጅ ሊሆን እንደማይችል ጠቅሰው፣ ዋናው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዘንድ መልካም ስነምግባርን ተከትሎ መስራትና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ የሚሰሩ ስራዎች ላይ መድረኩ ሊያተኩር የሚገባ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ በላይ ከአቪሲ ኔትወርክ ኢትዮጵያ፤ የድርጊት መርሃግብሩ ላይ "ቢያንስ" ይህን ያህል ተግባራት ይከናወናሉ ተብሎ ¾ተገለጹ ስራዎች መኖራቸውን ጠቁመው እነኝህ ግልፅ ያልሆኑ አገላለጾች ብኃላም ውጤታማነትን በምንለካት ጊዜ ሊያስቸግሩ ስለሚችሉ ቢስተካከል የሚል ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡ በጀትንም በሚመለከት ለአንዳንዶቹ ተግባራት የተተመነው የገንዘብ መጠን ያነሰ የሚመስል አለ ካሉ በኃላ፤ ስራው የሚጠናቀቅበትንም ጊዜ በተመለከተ አንዳንድ መዛባቶች እንደሚታዩ አስገንዝበዋል፡፡ በመጨረሻም ለንኡሳን ኮሚቴዎች የተሰጡት የስራ ድርሻዎች የድርጊት መርሃግብሩ ላይ ጎልተው እንዳልወጡ ገልጸው እንደገና ቢታዩ በማለት አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

አቶ ጌቱ ሙላቱ ከኔትወርክ ኦፍ ኦርጋናይዜሽንስ ኦፍ ዘ ቪዥዋሊ ኢምፔይርድ ኤንድ ብላይንድ (NOVIB) እንደጠቆሙት ምንም እንኳን ይህ መድረክ የቀድሞውን ግብረሃይል ሙሉ በሙሉ የሚተካ ባይሆንም፤ የቀድሞው ግብረሃይል ይሰጣቸው የነበሩትን ድጋፎች ማለትም የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን የመስጠትና የሀብት ማሰባሰብን የተመለከቱ ጉዳዮች በድርጊት መርሃግብሩ ውስጥ እንዳልተመለከቱ ገልጸዋል፡፡

አቶ ፋንታሁን መለሰ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ልማት ማህበራት ህብረት፤ በድርጊት መርሃግብሩ ውስጥ የተቀመጡት ተግባራት ብዙ መሆናቸውንና ስራዎቹ በንኡስ ኮሚቴዎች እንደሚሰሩ ጠቁመው፤ ውጤታማ ስራ ለመስራት የሚፈለግ ከሆነ የመድረኩ ጽ/ቤት በእጅጉ መጠናከር ይኖርበታል ብለዋል፡፡ ሀብት ማሰባሰብንም በተመለከተ ይህ ክፍል ለመድረኩ ህልውና ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፤ ለሀብት ማሰባሰብ ተብሎ የተመደበ ምንም አይነት በጀት አለመኖሩን ጠቁመው ይህ ስራ በምን መልኩ ሊሰራ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ሀብት የማሰባሰብ ስራ የሚሰራበትን ጊዜ በተመለከተ መጋቢትና ሰኔ ወራት ብቻ ነው የተቀመጠው ይህ ስራ ግን አመቱን በሙሉ መሰራት ያለበት ስራ መሆን እንዳለበት መገንዘባቸውን አሳውቀው ወይስ በእነዚህ ሁለት ወራት ላይ የተሰበሰበው ሀብት የመድረኩን የዓመት ስራ ማስኬድ ያስችላል በሚል እሳቤ ተወስዶ እንደሆነ ጠይቀዋል፡፡ በመቀጠል የጉባኤው አመቻች የሆኑት አቶ ሆሌ ፎሌ መድረኩን ተረክበው አስተያየት ሰጭዎችንና ተሳታፊዎችን በማመስገን፤ ብዙዎቹ የቀረቡት አስተያየቶች መሆናቸውን ጠቅሰው የመድረኩ ስራ አስፈጻሚዎች ወስደው እንደ ግብዓትነት እንደሚጠቀሙባቸው ቃል ገብተዋል፡፡ በመቀጠልም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ ዋና ጸሀፊ የሆኑትን አቶ ውብሸት ወ/ማርያምን ተጨማሪ ምላሽና አስተያየት እንዲሰጡ ወደ መድረክ ጋብዘዋል፡፡

አቶ ውብሸት የአቶ ሆሌን ሀሳብ በመጋራት ብዙዎቹ ከቤቱ የተሰነዘሩት ሀሳቦች ገንቢ አስተያየቶች መሆናቸውን ጠቁመው የድርጊት መርሃግብሩንም ለማሻሻል አበረታች መሆናቸውን ሳያስምሩበት አላለፉም፡፡ እቅዱ በዝቷል ተብሎ የቀረበው ስጋትን በሚመለከት ምንም እንኳን የድርጊት መርሃግብሩ ላይ የተመለከቱት ተግባራት ብዙ ቢሆንም ቅሉ ይህንን ተግባራት የሚያከናውኑት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ብቻ ሳይሆን የመድረኩ አባላት፣ ንኡስ ኮሚቴዎቹና የመድረኩ ጽ/ቤት እንደታሰበው የሚደራጅ ከሆነ የጽ/ቤቱ ሰራተኞች ድጋፍ ቀላል አይሆንም ብለዋል፡፡ ስለዚህ ይህ የድርጊት መርሀግብር እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ የስነምግባር ደንቡን በተመለከተ የተሰጡት አስተያየቶች ትክክል ናቸው ብለው፤ በተጀመሩ ስራዎች ላይ ተመስርቶ ቀጣይ ስራዎች እንደሚሰሩና ይህንን ታሳቢ አድርገው የስነምግባር ደንቡ ላይ እንደሚካተቱ ገልጸዋል፡፡ በዚህም ረገድ የስነምግባር ደንቡን በማስተዋወቅ፣ በመድረኩ አባላት ዘንድ ያለው ተፈጻሚነትን በሚመለከትና በሌሎችም መስኮች ላይ የቀረበውን አስተያየት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚገባ እንደሚያጤነው ተናግረዋል፡፡ በጀትን በተመለከተ የቀረበውን ጥያቄ ሲመልሱ መጀመሪያም በገለጻው እንደተጠቀመው የተመደበው ገንዘብ ግምት በጀት መሆኑን አስታውሰው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት እያንዳንዱ ተግባር በዝርዝር ባለመቀመጡ ምክንያት መሆኑን ጨምረው አስረድተዋል፡፡ ሀብት ማሰባሰብን በተመለከተ ቀድሞውንም የተሰሩ ስራዎች መኖራቸውን አስታውሰው በዚህም ወቅት የተዘጋጁ የተለያዩ ፕሮፖዛሎችና ኮንሴፕት ኖቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የዚህ የድርጊት መርሃግብር እውን መሆን በሚገኘው ሀብት መጠን ላይ የተመሰረተ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው ገልጸዋል፡፡ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በሚመለከትም የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሰፊው የተነጋገሩበት መሆኑን ጠቁመው፣ ይህም ተግባር በህብረቶችና ጥምረቶች እየተተገበረ ያለ እንደመሆኑ መጠን መድረኩ ይህን መሰል ተግባር ላይ ቢሰማራ ድግግሞሽ ከመፍጠር ያለፈ ጥቅም ሊኖረው እንደማይችል በመናገር ሃሳባቸውን አጠናቀዋል፡፡ በመቀጠል ተጨማሪ ሀሳብ የሰጡት አቶ ሆሌ ፎሌ ሲሆኑ እንደ እርሳቸው አገላለጽ በአቶ ጥጋቡ የቀረበው የመድረኩን ራዕይ የተመለከተውን ጥያቄ በድጋሚ አንስተው የመድረኩ ራዕይ ግልጽ ሲሆን ይህም ይህች ሀገር አድጋ ዜጎቿ የተሻለ ኑሮ ሲመሩ ማየት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ሀሳብ እስትራቴጂክ እቅዱ ሲጠናቀቅም እዚያ ላይ በግልፅ የሚካተት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የድርጊት መርሃግብሩን ተግባራት በቅደም ተከተል ማስቀመጡና እነኝህንም ተግባራት ካሉት ነባራዊ ሁኔታዎች አንጻር ሊሰሩ የሚችሉትን በመለየት አድምቶ መስራቱ አስፈላጊ ነው ተብሎ የተሰጠውን ሀሳብ እንደሚጋሩ ተናግረዋል ፡፡ በመጨረሻም በተከበሩ አቶ መሰረት የተሰጡትን ማሳሰቢያዎች ወሳኝነት በማጉላት፤ የስነምግባር ደንቡ በሕብረቶች አማካኝነት እያንዳንዱ በጎ አድራጎት ድርጅትና ማህበር ሰራተኞቹ እንዲያውቁት ሊያደርግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በዚህም በድርጊት መርሃግብሩ ላይ የተደረገው ውይይት ተጠናቆ ቤቱ ወደ ቀጣዩ አጀንዳ ተሸጋገሯል፡፡

## 3.4. የመድረኩን አርማ ለጉባኤው ማቅረብና  ውይይት በማድረግ የማጽደቅ ሂደት

በመድረኩ ሊቀመንበር አቶ ነጋሽ ተክሉ አማካኝነት የመድረኩን ራዕይና ተልዕኮ ሊያሳዩ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው አርማዎች በሁለት አማራጮች ለጉባኤው ተሳታፊዎች ቀርበዋል፡፡ አቶ ነጋሽ እያንዳንዱን አርማ ጥልቀት ካለው ገለጻ ጋር ለተሳታፊው በማቅረብ በጉባኤው ውሳኔ እንዲሰጥበት መድረኩን ለውይይትና ለጥያቄዎች ክፍት አድርገዋል፡፡
የመጀመሪያው አርማ እንደ አቶ ነጋሽ አገላለጽ አረንጓዴ ቀለም ያለው የኢትጵያ ካርታ ላይ እርስ በእርስ የተያያዙ እጆች የሚታዩበት ሲሆን ይህም በአረንጓዴ ዘንባባ የታጀበና “ኢትዮጵያን ፌዴራል ቻሪቲስ ኤንድ ሶሳይቲስ መድረክ” የሚል የእንግሊዘኛ ጽሁፍ ያለው ነው፡፡ የዚህ አርማ አጠቃላይ ትርጓሜው ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ልማት በጋራ የምንተጋ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ነን የሚል መሆኑን አመልክተዋል፡ ፡ እርስ በእርስ የተያያዙት እጆች ደግሞ “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” እንዲሉ ለጋራ አላማ መተባበርን መተጋገዝን ጠንካራ ጉልበትና ሀይል ይወክላሉ ለማለት ነው ብለዋል፡፡ በተጨማሪም አረንጓዴ የኢትዮጵያ ካርታ አረንጓዴ ዘንባባ በልማት ጎዳናና ብልጽግና ለምልማ ለማየት የምንናፍቃትን ኢትዮጵያን የሚወክል ነው ይህም ሀገሪቱ የመካከለኛ ገቢ  ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገው ጥረት ላይ በጎ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያለመ ስብስብ መሆኑን ያመለክታል ብለዋል፡፡

ሁለተኛውን አርማ በተመለከተ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለም ያላቸው የሰው ምስሎች በመያያዝ የከበቡዋት በባንዲራ የምትመሰለውን ኢትዮጵያን ሲሆን የመድረኩንም ስም የያዘ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ የዚህ አርማ ትርጓሜም የተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን የሚወክሉ ሲሆን እጅ ለእጅ መያያዛቸው ህብረት መፍጠራቸውን፣ ለጋራ አላማ መቆማቸውን፣ መተባበራቸውን፣ ማበራቸውንና መድረክ እንደመሆናቸው ለውይይትና ለምክክር መዘጋጀታቸውን የሚያመላክት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ከአረንጓዴ ቢጫና ቀይ ቀለማት ካላቸው የሰው ምስሎች ስር የሚታየው ግራጫማ ምስል ጥላቸው ሲሆን፤ ጥላቸው የሚያመለክተው ተጋግዘው ሀገሪቱን ካቋብዋት ሰዎች ስር የዚህ መድረክ አላማ ያሰባሰባቸው ጥላ የሆናቸውን ሌሎች አያሌ ዜጎችን ነው ብለዋል፡፡ አለም ክብ ናት በራሷ ዛቢያና በጸሀይ ዙርያ ትዞራለች ያሉት አቶ ነጋሽ የምስሎቹ መያያዝ የሚፈጥሩት ክብ መሰል ቅርጽ ሽክርክርነትን እንቅስቃሴን ለመወከል ያለመና ዘላቂ ልማት የማያቋርጥ የጋራ እንቅስቃሴ ውጤት መሆኑን ለማመላከትም ጭምር ነው በማለት ሰፋ ያለ ማብራርÁ ሰጥተዋል፡፡

በመቀጠልም ከጉባኤው ተሳታፊዎች ገንቢ አስተያየቶችና የተለያዩ ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል፡፡ የመጀመሪው አስተያየት ሰጪ አቶ ወንዱ በቀለ ከኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ማህበራት ህብረት (CENCEDA) ሲሆኑ ሁለቱም አርማዎች ጥሩ መሆናቸውን ገልጸው በአርማዎቹ ላይ የሚገኘው የመድረኩ ስም በእንግሊዘኛ ብቻ ከሚሆን ይልቅ አማርኛም ቢጨመረበት የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ሌላ ተሳታፊም በተመሳሳይ መልኩ የአቶ ወንዱን ሀሳብ የደገፉ ሲሆን፤ በተጨማሪም አርማው የመድረኩን ራዕይና ተልዕኮ የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን ሶስት ዋና ዋና ነገሮችን መያዝ ይኖርበታል ብለዋል፡፡ እነኝህም አንደኛ ትብብርንና በህብረት መስራትን እንዲያሳይ ሁለተኛ ሀገራዊ ልማትን የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል በሶስተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ሽግግርንና ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ ልማት የምታደርገውን ሽግግር ማሳየት አለበት ብለው እንደሚያምኑ አስገንዝበዋል፡፡ ስለዚህ የተያያዙት እጆች ትብብርንና ህብረትን የሚሳዩ እንደመሆናቸውና አረንጓዴው ሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴውን እንደማጉላቱ መጠን በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚያሳይ ምልክት ቢጨመርበት የመጀመሪያው አርማ እጅግ ተመራጭና ግልጽ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አቶ ዳምጠው አለሙ የተባሉ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ የመጡ ተሳታፊም አርማ ለማንኛውም ሰው ግልጽና በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል መሆን አለበት ብለዋል፡፡ ሁለተኛው አርማ በጣም ረቂቅነት ያለውና ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ  ለተለያየ ትርጓሜ የሚያጋልጥ ሲሆን የመጀመሪያው አርማ ላይ የመድረኩ ስም በአማረኛ ከላይ ተጨምሮበት ቢጸድቅ መልካም ነው ብለዋል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት የተከበሩ አቶ መሰረት ገብረማርያም በሌሎቹ ተሳታፊዎች የተሰጡትን አርማው ቀለል ያለና ግልጽ መሆን አለበት የሚለውን ሀሳብ እንደሚጋሩ ገልጸዋል፡፡ በተለይም በአርማው ላይ የመድረኩ ስም በአማረኛም እንዲጨመርበት የቀረበውን ሀሳብ በጽኑ እንደሚደግፉ ተናግረዋል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩ በአስተያየታቸው አረንጓዴ ቀለም ያለው የኢትዮጵያ ካርታ በአረንጓዴ ዘንባባ ታጅቦ መቅረቡ ላይ ያላቸውን ስጋት ገልጸው፤ ይህም አረንጓዴ ማለት ልምላሜንና መብቀልን ነው የሚያሳየው ገብስ ነው ወይም ስንዴ ነው ከተባለ ፍሬው ጉልህ ሆኖ አይታይም እየተመለከትን ያለነው ቅጠል ብቻ ነው ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ከኢንዱስትሪ እድገትና ቴክኖሎጂያዊ እመርታን ከማሳየት አንጻር የወደፊት ራዕያችንን የሚገልጽ ነገር ቢጨመር በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል፡፡

አቶ ነጋሽ ተክሉ በቀረቡት አስተያየቶችና ጥያቄች ላይ በመመርኮዝ እንደ መድረኩ ሊቀመንበርነታቸው ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፤ እንደ እርሳቸው አባባል በአብዛኛው የቀረቡትን አስተያየቶች በወሳኝ መልኩ እንደሚቀበሏቸውና ጠቃሚ ሀሳቦች መሰንዘራቸውን ጠቁመዋል፡፡ አርማው ላይ የመድረኩ ስያሜ በአማረኛ እንደሚካተትም አረጋግጠው ቴክኖሎጂ ሽግግርንም የሚወክሉ ምልክቶችን በመጨረሻው የመድረኩ አርማ ላይ እንደሚገባ ቃል ገብተዋል፡፡

በመጨረሻም የጉባዔው አመቻች የሆኑት አቶ ሆሌ በአርማው ዙርያ የቀረቡትን አስተያየቶች በሙሉ የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ እንደ ቤት ስራ ወስዶ በመጀመሪያ የቀረበውን አርማ አሻሽሎ እንደሚያቀርብ ቃል በመግባት በአርማው ዙርያ የተደረገውን ውይይቱ ተቋጭተዋል፡፡

## 3.5. በጎደሉ የመድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የንኡሳን ኮሚቴ አባላት ምርጫ

በመድረኩ ውስጥ ኢትዮጵያዊ የሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ይወክሉ የነበሩት ወ/ሮ ሳባ ገ/መድህን ከኢትዮጵያ የሴቶች ማኀበራት ቅንጅት (NEWA) ረዘም ላለ ጊዜ በሀገር ውስጥ ባለመገኘታቸው ምክንያት በመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥና ከCSSWG ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ላይ የእነዚህ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ውክልና ማስጠበቅ እንዳልተቻለ ተጠቅሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያዊ ከሆኑት ማህበራት የተወከሉ ሁለት ግለሰቦች ለውድድር ቀርበዋል፡፡ እነኝህም አቶ ታረቀኝ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን እና አቶ ጥጋቡ ሀይሌ ከአለም የእርቅና የሰላም ግብረሰናይ ድርጅት ናቸው፡፡

ቤቱ ባካሄደው ድምጽ የመስጠት ሂደት አቶ ጥጋቡ ሀይሌ ከአለም የእርቅና የሰላም ግብረሰናይ ድርጅት ሰባት ሰዎችን ባቀፈው የመድረኩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ ኢትዮጵያዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን በመወከል እንዲያገለግሉ ተመርጠዋል፡፡

## የመድረኩ ንኡስ ኮሚቴ አባላት ምርጫ

በዝክረ ነገሩ ላይ እንደተመለከተው መድረኩ ሶስት ንኡሳን ኮሚቴዎች እንዳሉትና እነኝህም ምርምርና ውይይት፣ ማስተዋወቅና ተጠያቂነት እና አጋርነትና በትብብር መስራት የሚሉት ሲሆኑ፣ የእነኝህንም ኮሚቴ አባላት ምርጫ ከመድረኩ አባላት በተወጣጡ ግለሰቦች መካከል ተደርጓል፡፡

ማስተዋወቅና ተጠያቂነት ንኡስ ኮሚቴ አባላት
(Sub-Comitee for Promotion and Accountablity)

1. አቶ ገብሬ ተሾመ
   Federation of Ethiopian National Associations of Persons with Disabilities (FENAPD)
2. አቶ አይቻልም ጎሹ
   Consortium of Cristian Relief and Development Asociations (CCRDA)
3. አቶ እስማኤል አሊ
   Afar Pastorarist Development Asociation (APDA)
4. አቶ ታረቀኝ አብዱልጀባር
   Ethiopian Youth Federation
5. ወ/ሮ ቤተልሄም ጠንክር
   Network of Ethiopian Women's Asociations (NEWA)

አጋርነትና በትብብር መስራት ንኡስ ኮሚቴ አባላት
(Sub-Comitee for Partnership and Collaborative Engagement)

1. አቶ ወንዱ በቀለ
   Ethiopian Non-Communicable Disease Consortium (ENCDC)
2. አቶ ኤፍሬም ብርሃኑ
   Consortium of Youth Development Organizations In Ethiopia (CoYDoE)
3. አቶ ሙክታር አልዪ
   Ethiopian Youth Network Harar Branch
4. አቶ ቴዎድሮስ በላይ
   Orphaned and Vulnerable Children (OVC) Network-Ethiopia
5. ወ/ሮ ፋጡማ ጀማል
   NOSP

ምርምርና ውይይት ንኡስ ኮሚቴ አባላት
(Sub-Comitee for Research and Dialogue)

1. አቶ ይፍክር ተፈራ
   Ocupational Safety and Health Professionals Association in Ethiopia (OSHPA-E)
2. አቶ ጌቱ ሙላቱ
   Network of Visually Impaired and the Blind (NOVIB)

3. አቶ ያዕቆብ አህመድ
   Pastoralist Development Network (PDN)
4. አቶ ብሩክ ከበደ
   National Podoconsis Action Network (NaPAN)
5. ወ/ሮ አዜብ መስፍን
   Ethiopian Women Federation (EWF)

## 3.6. በኢፌዲሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተዘጋጁ ወጪ መጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

በኢፌዲሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ የተዘጋጀው ወጪ በመጋራት የበጎ አድራጎት አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ ልዩ መመሪያ ቁጥር 1/2006 እና የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ላይ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ መሰረት ገብረማርያም ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ መመሪያ ቁጥር 1/2006 የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለሚሰጡት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት በዘላቂነት እንዲሰጡ የአገልግሎት ወጪን በማሳለጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለውን አሰራር ለመዘርጋት የህግ ማዕቀፍ ማበጀት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የተዘጋጀ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ በመቀጠልም በተከበሩ በአቶ መሰረት የቀረበው የዜጎች ቻርተር ረቂቅ ሰነድ ሲሆን ይህም ሰነድ ተገልጋይ ደንበኞች ከኤጀንሲው ማግኘት ስለሚገባቸው አገልግሎቶችና



የኢፌድሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ መሰረት ገብረማርያም ስለመመርያውና ረቂቁ ማብራሪያ ሲሰጡ

የአገልግሎት ደረጃዎች የሚያትት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በቻርተሩ ውስጥ እንደተጠቀሰውም የዚህ ሰነድ ዋና አላማ ከሆኑት መካከል የዜጎች መረጃ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ፣ ለዜጎች ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠትና ብሎም ተጠያቂነትን በግልጽ ማመላከት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የኢፌድሪ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ መሰረት ገብረማርያም በጉባኤው መዝጊያ ንግግራቸው ወቅት እንደጠቆሙት ይህን መሰል መድረኮች ለውይይትና ገንቢ ሀሳቦች መንሸራሸር ወሳኝ መሆናቸውን ገልጸው፣ ሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የውስጥ አቅም ለመፍጠር በትኩረት መስራት እንዳለባቸውም ጨምረው አሳስበዋል፡፡

ጉባኤው 10፡30 ሲሆን በመልካም መግባባትና በጥሩ ውጤት ተጠናቋል፡፡

# ጉባኤው በፎቶ









# Statute of the "Ethiopian Federal Charities and Societies Forum"

## Background

An active, informed and organized citizenry can substantially contribute to a mature and stable democracy. Charities and societies have an important role to play in reducing poverty, deepening democratic processes and promoting accountability. They can also offer alternative perspectives, opening space for poor, marginalized and vulnerable women, men and children to articulate their priorities, demands and opinions.

It is acknowledged that many of the gains achieved in poverty reduction and other areas in the last half decade were due in part to the contributions of Governments, private and ChS these days not only work closely with but also recognize the strong support of ChS and their contributions to the development effort. ChS have gained strong recognition and support from the donor community too.

As such the responsible government organs duly acknowledge the fact that facilitating and supporting initiatives of collaboration and cooperation among stakeholders is immensely instrumental to develop the best possible foundation for successful outcomes and visible impacts to be commonly achieved in relation to attainment of national goals and objectives in general and specific goals pertaining to the charities and societies sector. Putting it differently the absence of institutional arrangements ensuring participation of Charities and Societies in the development endeavors of this nation dictate putting in places the necessary frameworks creating operating environment conducive for involvement of all members of Charities and Societies.

That being the case in a bid to gain the maximum advantage from such commitment from the public sector, there is a need to reinvigorate the collaborative engagements of members of Charities and Societies through strengthening the existing structural arrangements and working procedures as well as ensure effective linkage is created between the sector and the relevant governmental stakeholders. This necessitates the establishment of a Forum for cooperation, coordination and collaborative engagement, consisting of Charities and Societies, which is found out to be highly instrumental towards the efforts to create a more enabling environment for Charities and Societies affairs. Accordingly, statute for this Forum is planned to be drafted and presented for endorsement by a consultative meeting of Charities and Societies operating in different parts of the country.

This is, therefore, a statute, which lays out the objectives, scope of engagements, organizational structure and working modalities of the Forum.

### Article 1
### Nomenclature

The full name of the collaborative framework shall be "Ethiopian Federal Charities and Societies Forum"

### Article 2
### Establishment

1. The Forum is established according to this statute: The legal personality of this Forum is derived from a special recognition provided by the Federal Charities and Societies Agency.

2. Charities and societies registered as local, resident and international represented by consortiums/ netwoks and a group of associations outside the consortiums/netwoks representatives are the basis.

## Article 3
## Purpose of establishment:

The main Purposes of establishing the Forum are:

➤To establish a formal non-statutory institutional arrangement whereby Charities and Societies participate in coordinating, cooperating, collaborating, facilitating and supervising a range of initiatives aimed at creating a more enabling environment for their effective engagement in national and international development endeavours.

➤To ensure effective administration, management and representation of the affairs of Charities and Societies operating in Ethiopia at all levels of engagement.

➤To put in place a foundation for the establishment of the necessary arrangements guiding the interactions between members of Charities and Societies and the relevant organs of the government as well as other development actors including donors and the private sector in accountable and sustainable manner.

## Article 4
## Roles and responsibilities of the Forum

In general, the Forum shall mainly be responsible for facilitating the collaborative engagements of Charities and Societies towards the creation of the necessary systems and infrastructures conducive for the affairs of as well as meaningful participation of Charities and Societies in the development of the nation. More specifically, it shall be responsible for;

1. Facilitate the establishment of an enabling environment regarding the affairs of Charities and Societies at all levels of engagement.

2. Promote the value of vibrant and effective Charities and Societies for bringing about sustainable development of the country.

3. Create information and knowledge base on all pertinent issues of Charities and Societies at comparative and national levels.

4. Facilitate experience and information sharing Forums among different stakeholders from the public, donors' community and representatives of Charities and Societies aimed at effective dialogue and coordination regarding the enjoyment of an enabling environment for the sector.

5. Facilitate effective partnership between Charities and Societies and different sector offices of the government.

6. Design and facilitate realization of efforts aimed at putting in place an effective system for following up, monitoring and evaluation of the activities of the Forum regarding creation of an enabling environment for Charities and Societies sector.

7. Design and adopt a code of conduct at which Charities and Societies can operate in an ethical and accountable manner.

## Article 5
## Membership of the Forum

1. In principle, membership is open to all Consortium/Networkss of Charities and Societies legally registered and operating in Ethiopia both at federal and regional levels.

2. Notwithstanding the above principles on membership the Forum should as much as possible strive to avoid multiple representation of Charities and Societies in the Forum by ensuring individual organizations representation through their networks/consortia.

3. Notwithstanding the above principle on membership of the Forum, emphasis shall be given for

representation of Charities and Societies that are working in regions where there is no or are not organized under Consortium/Networks by their representatives. Accordingly, 10-35 Charities and Societies will be represented by one organization while, more than 35 organizations will be represented by two elected organizations.

4. The Forum executive committee members and the secretariat will facilitate the process of electing representative.

**Article 6**
**Duties and responsibilities of members of the Forum**

1. Members shall be committed to the objectives of the Forum and make the priorities of the Forum match their own and see the Forum as adding value to their work.

2. Members shall be ready to make meaningful contributions in the efforts to coordinate and facilitate best and evidence based practice with regard to representation, promotion, and recognition of the Charities and Societies Sector.

3. Members shall be committed and effectively participate in the efforts of the Forum to facilitate information flow, communication and collaborative engagement for concerns and issues relevant to the creation of an enabling environment.

4. Members shall regularly attend meetings to review the effectiveness and efficiency of the activities of the Forum, to share information, update process, working procedures and enhance working relationships with government as well as between the member organizations involved.

5. Members shall carry out roles and responsibilities on voluntary basis.

6. Consortium/Networks members and group representatives of the Forum are responsible to breach and channel information, concerns and good practices from members to the Forum and from the Forum to members.

**Article 7**
**Delegation**

1. Its Executive Director shall represent each member Organization of the Forum.

2. The organization may delegate in writing a representative from the Organization to attend meetings of the Forum on the Organization's behalf.

**Article 8**
**Organizational Structure of the Forum**

The Forum shall have the following organizational structure, roles and responsibilities shared in the manner mentioned in the following articles

a. A convention comprised of all members of the Forum
b. Executive Committee
c. Sub Committees
d. Secretariat

**Article 9**
**Powers and Functions of the convention of the Forum**

The Convention, which is formed by all members of the Forum, is the supreme organ of the Forum with the following powers and responsibilities;

a. Elect and remove members of the Executive Committee;

b. Consider and approve annual work plan and program, project proposals, and budget submitted by

the Executive Committee and monitor the implementation.

c. Approve audit work and financial report submitted by the Executive Committee.

d. Determine its directions and strategies, inline with the objectives and functions of the Forum.

e. Issue guidelines on its future size, modalities of appointment and removal of its subsequent members.

f. Devise ways and means of generating the necessary financial and material resources for the implementation of its activities.

g. Approve policies as well as make amendments to this statute when deemed necessary and submitted by the Executive Committee.

h. Perform such other tasks that it may deem are relevant to the attainment of its objectives.

## Article 10
## Convention Meetings and Procedure for decision-making

1. The regular meeting of the convention shall be held on by-annual basis.

2. An extraordinary meeting may be convened at the request of the Executive Committee or one-third of the members of the Forum.

3. A quorum shall be constituted when more than half of the members of the Forum are present. Another meeting shall be called when a quorum is not constituted. Quorum shall be deemed to have been constituted by the second meeting regardless of the number of members present.

4. Decisions are passed based on a simple majority vote.

5. The following decisions shall be passed only on the basis of a two-third majority of members of the Forum:

a. Amendment of the statute of the Forum
b. Decision to dissolve the Forum
c. Admitting additional members of the Forum

## Article 11
## Organizational Structure of the Executive Committee

1. The Forum shall have the following Executive members, to be elected by the convention.

a. A Chairperson
b. A Deputy Chairperson
c. Three /Representatives of sector working group/and
d. Two Other members

2. Seven Executive members shall constitute the Executive Committee of the Forum.

3. The coordinator of the secretariat will serve the executive committee members as a secretary having no vote.

4. The Executive committee members to represent CSOs of the country at Federal, Regional and international level as much as possible the three categories of Charities and Societies (Resident, Ethiopian Charities and societies and foreign charities) shall be represented.

5. Only members of the Forum shall be elected for a three years term of service to the positions indicated under this Article.

6. An Executive Committee member can't be elected and serve in that capacity beyond an additional

three years term of office.

7. The Executive Committee members shall be accountable to the Convention.

8. The Executive Committee shall meet regularly every month.

## Article 12
## Powers and Functions of the Executive Committee

The Executive Committee shall have the following powers and functions:

1. Closely monitor and supervise the day- to-day activities of the Forum.

2. Provide guidance and supervision regarding the management and administration of the human and financial resources of the Forum.

3. Take the leadership in the preparation of the policy, strategic and operational plans, budget and periodic work plans of the Forum and submit it to the Convention for approval.

4. Represent the Forum at the national and international level and be speaker of the Forum.

5. Perform other tasks delegated to it by the decision of the convention of the Forum.

## Article 13
## The Chairperson

The Chairperson shall have the following duties and responsibilities;

a. In consultation with the Executive Committee, members ensure effective representation of the Forum in dealings and dialogues with all relevant stakeholders.

b. Convene and preside over the meetings of the Executive Committee and the Forum.

c. Closely monitor and supervise the day-to-day activities of the Forum including signing of correspondences.

d. Shall see to it that decisions passed by the Executive Committee are timely transmitted to the convention of the Forum.

e. Take the lead in the preparation and submission of draft policies, strategies and directives of the Forum for approval and ensure their implementation in a consistent manner.

f. Coordinate and follow up activities assigned to other members and structural set ups of the executive committee.

g. Prepare and present by annual report to the Convention of the Forum on the progress of the implementation of the planned activities.

h. See to it that the necessary facilitations and logistical support to the Forum, including arranging meetings and facilitation of partnership with key stakeholders, delivery of invitations and notices to members of the Forum, provision of meeting halls, and networking support.

## Article 14
## The Deputy Chairperson

The deputy Chairperson shall:

1. Discharge the duties and responsibilities of the Chairperson, in the absence of the later.

2. Provide overall supervision to the sub committees formed by the convention.

3. Undertake other tasks as assigned by the Executive Committee.

## Article 15
## Meetings of the Executive Committee

1. The Chairperson, or in his absence the deputy Chairperson might call extraordinary meetings of the Executive Committee.

2. The Voting Procedure stipulated under Article 12 shall also apply mutatis mutandis to Executive Committee meetings. Where there is a tie in voting during the executive committee meetings the chairperson shall have a casting vote.

## Article 16
## Sector working group representatives of the members of the Executive committee

The sector working group representatives, which comprise representatives from the three categories of Charities and Societies as, indicated above and that shall be members of the Executive Committee shall have the following roles and responsibilities

a. Take the primary responsibility to effectively represent the Forum in formal dialogue and lobbing Forums established by the government at federal levels.

b. Even if, the sector working group representatives are elected from the three categories of Charities and Societies, they shall be representatives of the Forum, not their respective category of charities and societies, at the secter working group.

c. In consultation with the Executive Committee, devise strategies ensuring effective participation of the Forum in formal dialogue sessions established by donors and the Federal Government.

D. Prepare and submit agendas pertain in to the charities and societies in the CSSWG

E. Prepare feedbacks in relation to participation in the formal dialogue Forums at Federal levels and submit it to the meetings of the Executive Committee of the Forum.

## Article 17
## Organizational structure of sub-committees

1. In view of the various objectives of the Forum, three Sub-Committees for promotion and accountability, Partnership and collaborative engagement with government and different stakeholders, and research and dialogue shall be established by the convention and each shall comprise three members of the Forum.

2. Each sub-committee will consist of five Forum members.

3. The three sub-committees shall be chaired by a member elected by the sub-committee meeting, under the overall supervision of the vice president of the Executive Committee.

4. Each chairperson of the sub-committee shall be responsible for the designing, implementation, coordination, periodic reporting, monitoring and evaluation of activities of the respective sub-committee

5. Assignment of members to the different sub-committees shall be made by the convention based on potential contributions to be made by the organizations in relation to any aspects of creation of an enabling environment and written consent of the latter to the assignment.

## Article 18
## Roles and responsibilities of sub-committees

The three sub-committees of the Forum shall have the following roles and responsibilities :

1. Sub-committee for promotion and accountability

This sub-committee shall have the following roles and responsibilities;

➤Develop common strategy, themes, issues and messages for lobbing, advocacy, recognition, representation and promotional activities in relation to the civil society sector in general and establishment of an enabling environment to Charities and Societies in particular.

➤Provide the necessary assistance to the secretariat and the executive committee in the development of communication plans specifically applicable to implementation of promotional activities and ways to enhance accountability.

➤Help in the identification of appropriate strategies and media outlets for the promotion of the Charities and Societies sector and creation of an enabling environment for the same.

➤Ensures more comprehensive and consistent emphasis is given to the sustaining of an enabling environment in coverage of issues relevant to the charities and societies sector.

2. Sub-committees for partnership and collaborative engagement

This sub-committee shall have the following roles and responsibilities;

➤Assess ways to create linkage between members of the Forum at national, regional and local levels.

➤Provide guidance and supervision in relation to facilitating consultations and information sharing with donors, government line ministries and other pertinent stakeholders

➤Provide the necessary assistance in the development of appropriate strategies and other modalities for partnership with a view to enlarging space for Charities and societies in formal as well as informal dialogue Forums of donors and respective government bodies

➤Help in the designing of appropriate tools for developing improved multi-sectored partnership among members of the Forum as well as encourage potential partners to join efforts to effectively promote the creation of an enabling environment for the operation of civil societies in Ethiopia.

➤Assist in the designing of an action plan specifically applicable for the implementation of activities in relation to facilitation dialogues with different stakeholders including the government.

➤See to it that improved access to evidence based approaches and understanding of the needs and priorities of the sector as well as existing knowledge and practice at international and national level in the area of strategic government and civil society partnership are availed to the responsible organs of the platform representing it at the sector working groups.

3. Sub-committee for research and dialogue

This sub-committee shall have the following roles and responsibilities;

➤Assist in the development of appropriate strategy and other mechanisms and action plans for effectively promoting an inclusive multi-stakeholders approach in relation to the creation and sustaining of an enabling environment.

➤Advise in identifying timely and appropriate research priorities for the charities and societies sector.

➤Devise ways for dissemination and discussion of major research findings.

➤Hold consecutive high-level dialogues to improve the operation of charities and societies in the country.

Facilitate the presentation of evidence-based arguments to increase the participation of charities and societies in the overall national development.

## Article 19
## Powers and functions of the Secretariat of the Forum

The Forum shall have its own Secretariat, which is to be headed by a Coordinator, and shall:

1. Carryout the day-to-day activities of the Forum in accordance with periodic plans approved by the convention and under the direction of the Executive Committee of the Forum.

2. Provide the necessary assistance to the Executive Committee in the preparation of periodic plans and budgets of the Forum.

3. Record the minutes of the Convention of the Forum and the Executive Committee and transmit same for the secretary of the Executive Committee

4. Keep all the necessary documents of the Forum.

5. Handle the correspondence of the Forum under the direction of the Chairperson.

6. Ensure external correspondences of the Forum are signed and sealed by the chairperson of the executive committee and in his/her absence by the deputy chairperson of the Executive Committee.

## Article 20
## Auditing and Financial Administration

1. The Forum will have its own financial administration system and Bank Account.

2. The coordinator of the Forum shall authorize payments from the Forum's accounts by consulting the Executive Committee.

3. The properties and finance of the Forum acquired to implement its activities shall be maintained and administered in strict compliance with nationally accepted rules and principles of financial management.

## Article 21
## Amendments

This statute of the Forum may be amended, revised or repealed by a two third majority decision of the convention at any regular or special meeting, duly convened following notice to that effect.

## Article 22
## Effective Date

This Statute of the Forum shall be effective from 25th February 2014.

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ➢ Consult with members of the Forum and identify major common issues for representation.<br>➢ Organise consultation forums and meetings to raise, and hold discussions and negotiations with relevant government and other bodies, and platforms, such as CSSWG, on major issues identified in consultation with members of the Forum.<br>➢ Provide adequate and timely feedback to members of the Forum. | | | | | | | | |
| D | **Resource Mobilisation.** | | | | | | | | |
| 1 | Resource Mobilisation/fundraising to implement Action Plans of the Forum.<br><br>➢ Mapping of and networking with potential donors and relevant stakeholders.<br>➢ Developing and submitting Project Concept Notes and Proposals to potential donors.<br>➢ Discussion and negotiation with potential donors and securing funding resources. | XXXX | | XXXX | | | Ato Negash<br>Wro. Yetnebersh<br>Ato Wubeshet | March and June 2014 | Availability of funding |

# Ethiopian Federal Charities and Societies Forum
# Attendance Sheet
# 1st General Assembly Meeting
## February 25, 2014, Desalegn Hotel

| No | Name | Name of Organization |
|---|---|---|
| 1 | Negash Teklu | PHE-EC |
| 2 | Holie Folie | CoRHA |
| 3 | Giday Zerhun | MoFA |
| 4 | Tezera Getahun | PFE |
| 5 | Zinash Ketate | PANE |
| 6 | Tesfay Melaku | Light Ethiopia |
| 7 | Christine Seiffu | Eth. Society of Malaria |
| 8 | Chekole Kidane | CSSP |
| 9 | Thomas Huyghebaert | EU |
| 10 | Tiruwork Moges | EU |
| 11 | Tigabu Haile | AMPI |
| 12 | Ismal Ali | APDA |
| 13 | Bizu Ketete | Irish Aid |
| 14 | Abreham | Culture & tourism |
| 15 | Dessalegn Samuel | MoE |
| 16 | Alemayehu Diro | NECSO |
| 17 | Wondu Bekele | CENCDA |
| 18 | Ayichalim Goshu | CCRDA |
| 19 | Tewodros Belay | OVC Net |
| 20 | Elizabeth Mengistu | TCDN |
| 21 | Motuma Terfassa | Eth. Youth Federation |
| 22 | Addisu Desalegn | NBGPT |
| 23 | Yetnebersh Nigussie | ECDD |
| 24 | Wubeshet W/Mariam | VSO |
| 25 | Mesfin Tadesse | ChSA |
| 26 | Degene Teshome | ChSA |
| 27 | Tsedalework Gismu | ChSA |
| 28 | Yakob Ahmed | PDN |
| 29 | Bzayen G/her | CSHA |
| 30 | H/Selassie G/michael | CSHA |
| 31 | Tsehai Shiferaw | CSHA |
| 32 | Yoseph Ayalew | SLUF |
| 33 | Asfaw Kaba | APDF |
| 34 | Ambessie Wake | IRC |
| 35 | Alalewold Bantiyergu | EU-CSF |
| 36 | Gebray Teshome | Federation of Ethiopia Association Person with Disability |
| 37 | Damtew Alemu | MoLSA |
| 38 | Muktar Aliye | EYNHB |
| 39 | Biruk Kebede | NaPAN |
| 40 | Getinet Assefa | CSSP |
| 41 | Gemechu Desta | TECS |
| 42 | Tigist Abdeta | ChSA |
| 43 | Elias Assefa | ChSA |
| 44 | Asefa Tesfaye | ChSA |
| 45 | Yifokire Tefera | OSHPA |
| 46 | Getu Mulatu | NOVIB |
| 47 | Merhawit Muluberhan | NOVIB |
| 48 | Ephreme Berhanu | COYDCE |
| 49 | Fantahun Melesse | BGDAN |
| 50 | Ayelech Demissie | ENA |
| 51 | Yared Nigussie | The Daily Monitor |
| 52 | Birhanu W/Semayat | Fana Broadcasting Corporate |
| 53 | Tamirt Gezachew | Reporter Newspaper |
| 54 | Wudineh Zenebe | Reporter Newspaper |
| 55 | Lemlem Mengistu | Ethiopian Press Agency |
| 56 | Aduga Daba | ENA |

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Charities and Societies Agency

ቁጥር [illegible]
Ref. No

ቀን 14 ሰኔ 2005
Date

## ለሚመለከተው ሁሉ

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ተልእኮ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተደራጅተው በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት፣ ልማት እና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር በመዘርጋት በመመዝገብ ፈቃድ በመስጠት በመደገፍና በመከታተል የተጣለውን ሕጋዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ ተቋም ነው።

[illegible]

- [illegible]
- [illegible]
- [illegible]

[illegible]

በአባላቶችን በዚህ ዘርፍ የመጀመሪያው የሆነውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የፌዴራል መድረክ ዘርፉንና መንግስትን [illegible] [illegible] ቀላል ማይባል እገዛ ይሰጣል ብለን የሚያምንበት ሁኔታን እንዲፈጥሩ ጠቀሜታ እንደሚኖረው፣ በአባላትን ተጠቃሚነትና የአባላትን [illegible] በርካታ ግንኙነት ለመፍጠር የሲቪክ መንፈስ [illegible] በማከናወን [illegible] [illegible] እንቅስቃሴዎችን የሚደገፉ ስራ [illegible] በመተባበር [illegible] [illegible] አባላትን በዚህ ዘርፍ ስራዎች መንገዶች በሚፈለጉ አካላት [illegible] ውስጥና ከአገር ውጪም በዚህ ዘርፍ አባላትን በማስገባትና ጥሩ አርአያ ሆኖ ለመገኘት ተጨማሪ ጥቅም ይኖረዋል ተብሎ በማሰብ ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት [illegible] [illegible] [illegible] ሕጋዊ ድጋፍ ተደርጎለት የተቋቋመ የፌዴራል መድረክ መሆኑን እናረጋግጣለን።

ከሠላምታ ጋር

# Media Reflections



**Poised to reinvigorate charity, society roles**

**The Ethiopian Herald News of March 7/2014**

Historical evidences indicate that charities and societies first started to appear in Ethiopia in the 1950's and these were mostly of European origin. In the 1970's more NGOs [illegible] in response first to the 1973/74 famine and later on to the 1983/84 [illegible] continued to grow after the overthrow of the military re- [illegible] national and international Non- [illegible] for almost half a [illegible]

ድርጅቶቹ የልማት አጋርነታቸውን የሚያጠናክሩበት አደረጃጀት ተመሠረተ

አዲስ ዘመን

Written By [illegible]

Category: [illegible]

Design + Print PHILMON PRESS

**Ethiopian Federal Charities and Societies Forum (EFCSF)**
Phone: 0118675939 / 251-920-863714
Fax: 0116638127
E-mail: fcsf2005@gmail.com
info@fcsf.net
www.fcsf.net
Djibouti Street, behind St. Gabriel Hospital
P.o.Box: 4408 Addis Ababa, Ethiopia.